“ሞቶሙሰ ለጻድቃን ሕይወቶሙ ውእቱ፤
የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው።”
(ቅዱስ ያሬድ)

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ





ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ትውልዱ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር እንዲመልስ ያስተማሩ አባት ነበሩ

ካሳሁን ለምለሙ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ

አራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ትውልዱ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር እንዲመልስ ተግተው ያስተምሩ እንደነበር የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ተናገሩ። ቅዱስነታቸው ለትውልዱ የነበራቸው ቀና አመለካከት የሚጀምረው ተማሪ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ እንደነበረ የጠቀሱት ብፁዕነታቸው “ለትውልዱ ምሳሌ ለመሆንና ትውልዱ ራሱን ከእግዚአብሔር እንዳያርቅ በፈተና ውስጥ ሆነው በርካታ አገልግሎቶችን ፈጽመዋል” ብለዋል፡ ፡ ብፁዕነታቸው አያይዘው ቅዱስነታቸው ለምድራችን በረከት የሚያመጡ ትምህርቶችን ያስተማሩ መሆናቸውን ጠቁመው የዚህ ዘመን ትውልድም ከእርሳቸው የአገልግሎት ሕይወት ብዙ መማር እንዳለበት አንሥተዋል።

ቅዱስነታቸው ፍጹም የሆነ የብትሕውና ሕይወትን ሲመሩ የነበሩ፣ ደግና ለትውልዱ አዛኝ እንደነበሩ ብፁዕነታቸው ምስክርነታቸውን ከሰጡ በኋላ ለአመኑበት ነገር ሁሉ ቆራጥና ጠንካራ እንዲሁም ችግሮችን በቀላሉ የመፍታት መንፈሳዊ ብቃት የነበራቸው መሆናቸውን ተናግረዋል።

ቅዱስነታቸው ከመከፋፈል ይልቅ የሀገርንና የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ሰላም አጥብቀው የሚፈልጉ እውነተኛ አባት እንደነበሩ የጠቆሙት ብፁዕነታቸው ዝምታቸው እንኳን አስታራቂ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ በበኩላቸው ቅዱስነታቸው እወነተኛ መሪና አገልጋይ የነበሩ መሆናቸውን ተናግረው በችግር ውስጥ እንኳን ሆነው ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ይበልጥ ሠርተዋል፤ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋና ቤተ ክርስቲያን በውጭው ዓለም እንድትሰፋ ሐዋርያዊ ተልኳቸውን በብቃት ተወጥተዋል በማለት ተናግረዋል።

የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እንዲሁ ቅዱስነታቸው ከዚህ ዓለም ድካም ማረፋቸው እንዳሳዘናቸው ገልጠው የጸሎትና የበረከት አባት እንደነበሩም ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ቤተ ክርስቲያናችን አለኝ ከምትላቸው የሚወደዱና የሚከበሩ ሊቃውንት መካከል አንዱ መሆናቸውን የምሥራቅ ወለጋ፣ የሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣እና የምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ገልጠው ክፉና ደግ ላለመናገር በዝምታ የቆዩና ዓለምን የናቁ እውነተኛ ተሀራሚ አባት እንደነበሩ ተናግረዋል።

ብፁዕነታቸው አክለውም “ቅዱስነታቸውን የመሰለ የጸሎት፣የበረከትና የአርምሞ አባት ማጣታችን የሚያሳዝንና ብዙ ነገር የሚያጎድል ነው። በሕይወት ቢቆዩ ደግሞ ጸሎታቸውና በረከታቸው ይጠብቀን ነበር፤ ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በሥጋ ቢለዩንም ከምስጋና የበለጠ ወደ ምስጋና ስፍራ በመሄዳቸው ልናዝን አይገባም” ብለዋል። ቅዱስነታቸው ትጉህ፣ቆፍጣናና የውሳኔ ሰው ከመሆናቸው የተነሣ ለቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሉዓላዊነት አብዝተው የሚጨነቁ አባት እንደነበሩ የገለጡት ደግሞ የባሕር ዳርና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ናቸው።

ቅዱስነታቸው ከአባታቸው ከብላታ ፋንታ ተሰማ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ለምለም ለገሰ በጎንደር ክፍለ ሀገር ደብረ ታቦር አውራጃ አለታ ወረዳ ልዩ ስሙ ማር ምድር በተባለ አካባቢ በ፲፱፻" ዓ.ም መወለዳቸውን የግል ማኅደራቸው ያሳያል በተወለዱበት አካባቢ ሀረርት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ንባብና ዳዊትን ተምረዋል። ከዚያም ወደ አጭዳ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በማቅናት ምዕራፍ፣ድጓና ጾመ ድጓ ተምረዋል። ለተጨማሪ ትምህርትም ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር በማቅናት የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርረቶችን ቀስመዋል።

ወደ ዋሸራ ገዳም በማቅናትም የቅኔ ትምህርት ተምረው፣አቋቋምንና ዝማሬ መዋሥዕት ደግሞ በደብረ ታቦር አውራጃ አጠናቀዋል። በንፋስ መውጫ አውራጃ በታች ጋይንት እንዲሁ ድጓ አስመስክረው በመምህርነት ተመርቃዋል በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ደግሞ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መዓርገ ምንኵስና ተቀብለው በገዳማዊ አገልግሎት የቆዩት ቅዱስነታቸው በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴና በማኅሌት ሲያገለግሉ ቆይተው የሐዲሳትና የአቡሻኽር ትምህርት ተምረዋል። ከዚያም በኋላ በተለያዩ ገዳማትና አድባራት በአስተዳደሪነት አገልግለዋል።

በነበራቸው መንፈሳዊ ዕውቀትና አገልጋይነት የተነሣ በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ተብለው በኤጲስቆጶስነት ተሹመዋል። ከዚያም የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው እያገለገሉ በነበረበት ወቅት ሐዋርያዊ ተልኳቸውን በተሳካ ሁኔታ በመፈጸማቸው ነሐሴ ፳ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም አራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ተሹመዋል።

ከ፲፱፻፹ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም በፓትርያርክነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንን እያገለገሉ በነበሩበት ወቅት በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ሥርዓት ተገፍተው ሀገራቸውን ትተው ተሰደዋል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገራችን በመጣው የፖለቲካ ለውጥ ምክንያት ከ፳ዓመታት በላይ የስደት ቆይታ በኋላ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም ከስደት ተመልሰዋል። ቅዱስነታቸው ከስደት ወደ ሀገራቸውና መንበራቸው ከተመለሱ በኋላ በአገልግሎት ላይ እያሉ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው የካቲት ፳፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በ፹፬ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም ዐርፈው፣ መጋቢት ፬ ቀን ፲፻፲፬ ዓ.ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥርዓተ ቀብራቸው መፈጸሙ ይታወሳል።

# ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም ከዚህ ዓለም ድካም ዐረፉ

ሚኒልክ ብርሃኑ



ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም
(የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስነት)

ከ፴ ዓመታት በላይ የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከትን በሊቀ ጳጳስነት ሲመሩ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም ከዚህ ዓለም ድካም ዐረፉ፡፡ ብፁዕነታቸው ከእናታቸው ከወ/ሮ ሸዋ አነሰሽ ወልደ ሥላሴ እና ከአባታቸው ከአቶ ጸዳለ ክርስቶስ ገብረ ሃና በቀድሞው አጠራር ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ተጉለት ወረዳ ጭምብሬ ቀበሌ ውስጥ ልዩ ስሙ ውቅጤ ሚካኤል ከሚባል ቦታ ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፲፯ ዓ.ም ተወለዱ፡፡

ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ  ደብረ ሳህል ቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ከመሪጌታ ወልደ ጊዮርጊስ ፊደልን፣ ዳዊትን እና ሰዓታትን፤ ከመምህር ፍሬ ሰንበት ድጓን፣ ጾመ ድጓንና ምዕራፍን ተምረዋል፡፡ ወደ በጌ ምድርም በማቅናት ዙር አምባ ጽርሐ አርያም ገዳም ዝማሬ መዋሥዕት አጥንተዋል፡፡

ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም ትምህርት የበለጠ ለማጠናከር በመንዝ አውራጃ ጠዶበር ቂያ ዮሐንስ ከተባለው ቦታ ከመ/ር ኪዳነ ማርያም ቅዳሴን፤ በፍቼ ሰላሌ ስሬ መድኃኔ ዓለም ከአለቃ ጥበቡ ገሜ እና ተጉለት ከሚገኙት አለቃ ኃይሌ ዘንድ ቅኔ ተቀኝተዋል፡፡ በኢቲሳ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ከመሪጌታ ጌታሁን /በኋላ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የሲዳማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከሆኑት/ ለሦስት ዓመታት ተምረዋል፡፡ በመቀጠልም ወደ አዲስ አበባም በመምጣት ታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ገዳም መጻሕፍተ ሐዲሳቱን አጥንተዋል፡፡ ሦስተኛ በመውጣትም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ ሽልማት ተቀብለዋል፡፡

ብፁዕነታቸው በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ዲቁናን ከግብፃዊው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፤ በ፲፱፻፵ ዓ.ም ምንኵስናን ከአቡነ ማቴዎስ፤ ከጎጃም ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት አቡነ ማርቆስ ቅስናን ሲቀበሉ ቁምስናን ደግሞ ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል ተቀብለዋል፡፡ አገልግሎታቸውንም በሲዳማ አለታ ወንዶ ባለወልድ ቤተ ክርስቲያን በጃንሆይ ልጅ በልዕልት ተናኘወርቅ አማካኝነት ተመድበው አሐዱ ብለው ጀምረዋል፡፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በሚገኘው ደብረ በግዕ አቡነ ሕፃን ሞዓ ገዳም ተመድበው ለ፫ ዓመታት በመምህርነት  አገልግለዋል፡፡ ጥቅምት ፩ ቀን 1፲፱፻፷፱ ዓ.ም የበዓታ ነገሥት አስተዳዳሪ ሆነው በመሾም በርካታ አገልግሎቶችን ፈጽመዋል፡፡

ጥቅምት ፲፬ ቀን፣ ፲፱፻፸፪ ዓ.ም በብፁዕ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ ከተሸሙት ፲፰ ኤጲስ ቆጳሳት መካከል አንዱ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተሸመዋል፡፡ በአርሲ ቆታቸውም ብዙ ምእመናን አጥምቀው የሥላሴ ልጅነት እንዲያገኙ አድርገዋል በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀዋል፡፡ በ፲፱፻፸፰ ወደ ትግራይ ሀገረ ስብከት በመዛወርም ሰፊ ሐዋርያዊ አገልግሎትን ፈጽመዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የካቲት ፲፫ ቀን፣ ፲፱፻፹፲ ዓ.ም የሰሜን ሸዋ ደብረ ብርሃን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በመሆን እስከ ዕርግና ዘመናቸው ድረስ አገልግለዋል፡፡

ብፁዕነታቸው በረጅም ዓመታት የአገልግሎት ዘመናቸው ከ፫፻፷ በላይ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጸዋል፤ በግራኝ ተቃጥለው የነበሩትን በአዲስ መልክ አስገንብተዋል፤ ፈርሰው ነበሩትን ጥንታዊ ገዳማትን አሳድሰዋል፡፡ እንደ ቀደሙት አባቶች ብራና ዳምጠው፣ ቀለም በጥብጠው፣ ብዕር ቀርፀው መዝሙረ ዳዊትን፣ ቀሌምንጦስን፣ ገድለ ሐዋርያትን፣ ቅዱስ ወንጌልን፣ ቅዳሴ ማርያምንና ነገረ ማርያምን ራሳቸው ጽፈዋል፡፡

ብጹዕነታቸው ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በአዲስ አበባ ገሱንድ የሕክምና ማዕከል በሕክምና ሲረዱ ቆይተው የካቲት ፳፯ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በ ከዚህ ዓለም ድካም ዐርፈዋል፡፡ ሥርዐተ ቀብራቸውም ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ ወዳጅ ዘመዶቻቸው እና በርካታ ምእመናን በተገኙበት መጋቢት ፩ ቀን፣ ፳፻፲፬ ዓ.ም በጥንታዊው የደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡

# በሥራ የተገለጠ ልባዊ አንድነት ለቤተ ክርስቲያን

በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዐለትነት ላይ የተመሠረተችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮዋን ተቀብላ የክርስቶስን ወንጌል መስበክ ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ ፈተና ተለይቷት አያውቅም፡፡ ‹‹ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ለፍጥረትም ሁሉ ወንጌልን ስበኩ›› (ማር.፲፮፥፲፭) የሚለውን አምላካዊ ቃል ተሸክማ በዓለም ውስጥ ስትመላለስ ሐዋርያዊ ተልእኮዋን እንዳትፈጽም ብዙ እንቅፋቶች ገጥመዋታል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ‹‹...ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድኩ፤በወንዝ ፍርሀት፣ በወንበዴዎች ፍርሀት፣ በወገኔ በኩል ፍርሀት፣ በአሕዛብ በኩል ፍርሀት፣. . .›› ብሎ ከሚገልጠው ውስጣዊ ፈተና ጀምሮ በዐላውያን ነገሥታት እስከ ደረሰባት ውጫዊ ፈተና ቅደስት ቤተ ክርስቲያን ብዙ ዋጋን ከፍላለች፡፡

ቅዱስ ወንጌል ለዓለም እንዲደርስ ባደረገችው ሐዋርያዊ ጉዞ ውስጥ ከተቀበለችው ውጫዊ መከራ በባሰ መልኩ አንድነቷን የሚሸረሽር፣ የሚከፋፍላት ውስጣዊ ፈተናም በዚያው ልክ አስተናግዳለች፡፡ የክርስቶስን መስቀል ተሸክማ አገልግሎት የጀመረችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያዎቹ የሐዋርያዊነት ዘመናት ከቤቱ ሰዎች ከአይሁድ የደረሰባት ፈተና ቀላል የሚባል አልነበረም፡ ፡ በዘመነ ሰማዕታት ያሳለፈችው የሰቆቃ ጊዜ በብዙ ሰማዕታት ልጆችዋ ደምና አጥንት ወንጌል ለሚቀጥለው ትውልድ ቢተላለፍም እንዲህ ዓይነቱ ውጫዊ ፈተና ብዙ ዋጋ እንዳስከፈላት የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ሆኖም በየዘመኑ ይነሡ የነበሩትን ፈተናዎች በድል የተወጡት ክርስቲያኖች ከምእመን እስከ ታላላቆቹ አባቶች ውሳጣዊ አንድነት ስለነበራቸው ነው፡፡

በዘመነ መናፍቃን የቤተ ክርስቲያን ልጆች መስለው በእምነት ግን ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ባፈነገጡ መናፍቃን የቈሰለችውና ዛሬም ድረስ ያልሻረ ቊስል ሌላው የአገልግሎት እንቅፋት መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ በዚያ ዘመን የተነሣውን የመናፍቃን ፈተና ለማሸነፍ አባቶች ያሳዩት ብርቱ ተጋድሎ፣ ጽናት እና አንድነት ዛሬም ድረስ ለአብነት የሚነሣ ነው፡፡ እነ አርዮስን፣ መቅዶንዮስን፣ ንስጥሮስንና ሌሎችም መናፍቃን አውግዘው ለመለየት ምእመናንን በሃይማኖት ለማጽናት በየጉባኤው የተገኙት ቅዱሳን አባቶች እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ አሳቢ ነበሩ፡፡

በዘመን ሂደት እየተሸረሸረ የመጣው ኅብረት እና አንድነት ይልቁንም በብዙዎች ዘንድ ጎልቶ የሚታየው የቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ቤተ ክርስቲያን አሁን ላይ እየተቀበለች ላለው የከፋ ችግር ዳርጓታል፡፡ ባጋጠመው የመለያየት ሽንቁር ብዙዎች ገብተው ቤተ ክርስቲያን በአንድ በኩል የመንግሥትና የፖለቲካ ጥገኛ እንድትሆን በማድረግ የነበራትን ተሰሚነት፣ ክብር እና ኃይል አሳጥተዋታል፡፡ በሌላ በኩል ዳግም ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ ሌት ተቀን የማይተኙት መናፍቃን እንደ ልብ ዘው ብለው መሠረቷን እንዲነቀንቁ በር ከፍቶላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ላይ እየከፈለች ላለው ዋጋ እንዲሁም በየትኛውም ቦታና አጋጣሚ ተጎጂ እንድትሆን የነበረው መከፋፈል ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ሆኖም ትላንት የመጣንበትን መንገድ፤ በተለይ የቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ መከፋፈልና ከዚያ ጋር ተያይዘው የመጡ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ቤተ ክርስቲያን የከፋ ችግር እንዳይደርስባት አጥብቃ መሥራት ይጠበቅባታል፡፡

ሁሉም ባይሆኑ የተሰጣቸውን የቤተ ክርስቲያን አደራ ወደ ጎን በመተዉ ለራሳቸው ምድራዊ ክብር እና ዝና ሲሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍተት እንዲፈጠር፣ ከራሳቸው አልፎ ምእመናን እንዲከፋፈሉ፣ እንዲበተኑ ሲሠሩ የነበሩ ጥቂቶች ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ያላት ገጽታ እንዲኖራት፣ተቀባይነትዋ እንዲቀንስ አድርገዋል፡፡

ሆኖም እንዲህ ዓይነቶቹን መግራት፣ሥርዓት ማስያዝ፣ ማንነታቸውን ለምእመኑ በመግለጽ ስለ አንድነት በማስተማር ታች ድረስ የዘለቀውን የክፍፍል መንፈስ ማጥፋት ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ይጠበቃል።

ዘር፣ ቋንቋና ቀለም ሳትለይ ወንጌልን ለዓለም ያዳረሰች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ላይ በዘር አረንቋ ውስጥ መዘፈቋ ፤ ክፍፍሉ ከምእመናን እስከ ታላላቆች አባቶች መዝለቁ የቤተ ክርስቲያን የነገ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ነው የሚል ጥያቄን ያጭራል። ትውልዱን እየወረሰ ያለው የዘረኝነት መንፈስ የመጀመሪያ የጥቃት ዒላማውን ያደረገው በቤተ ክርስቲያን ላይ ነውና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በማስተማር በማንቃት፣ አርአያ ሆና በመታየት ኃላፊነቷን መወጣት አልፎ የሚሄደውንም ቢሆን አጥብቃ ልትቃወም፣ ልታወግዝ ጭምር ይገባታል። ከዚህም በተጨማሪ በአንድ የቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው እዚያና እዚህ በመሆን የተለያየ ሐሳብ በማራመድ ተከታይ ምእመናን የሚከፋፍሉ አካላት ሃይ የሚላቸው አካል ሊኖር ይገባል።

የውስጥ መከፋፈል እንደ ትልቅ ዕድል ቆጥሮ በደካማ ጎን በመግባት ይህችን ሐዋርያዊትና ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ለሚንቀሳቀስ የዘመኑ ጠላት ሁሉ ደካማ ጎንን አርሞ፣ በአንድነት በመቆም የቤተ ክርስቲያንን ቀጣይ ህልውና ማስጠበቅ ከቤተ ክርስቲያን ልጆች የሚጠበቅ የዘመኑ ሥራ ነው። እንዲህ ዓይነቶቹን እኩያን የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች አሳፍሮ ለመመለስ እና ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቀደመ ክብሯ ለመመለስ በቅድሚያ የራስ አንድነት፣ ኅብረት፣ መደማመጥ አስፈላጊ ነው። የሐሳብ ልዩነትን ከማስፋት ይልቅ በማጥበብ፤ ከመግፋት ይልቅ በመቅረብና በመቀራረብ አንድነትን አጠንክሮ መሄድ የቤተ ክርስቲያን ባህል ሊሆን ይገባል። እዚህና እዚያ በመሆን ጫፍና ጫፍ ይዞ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተለያየ ሐሳብ ማንጸባረቅ ራስን ለጠላት አሳልፎ ከመስጠት የዘለለ ዋጋ የሌለው መሆኑን አውቆ በአንድ ሐሳብ ለቤተ ክርስቲያን መሥራት ነገ ብሶ ከሚመጣው አደጋ ይታደጋልና ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል። በተለይም ቤተ ክርቲያን የተከፈተባትን ዘርፈ ብዙ ዘመቻ ለመቋቋም በመጀመሪያ የውስጥ አንድነት የእርስ በርስ ተግባቦት ላይ መሥራት እንደሚገባ ሊሰመርበት ይገባል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለችውን ሐዋርያዊ አስተምህሮ አንድነትን፣ ፍቅርን፣ መተሳሰብን በማስተማር እና በተግባር በመግለጥ በዘርና በቋንቋ እየጠፋ ላለው ትውልድ ብሎም ቤተ ክርስቲያንን እያጠፋ ላለው ሁሉ በማስተማር ሁሉም ወደ አንድ እንዲመጡ መሥራት ተገቢ ነው። በተለይም ቤተ ክርስቲያን እንደተቀበለችው የኖላዊነት ተልእኮ እንዲሁም አንድ እንደሆነው መዋቅሯ ሁሉ የልብ አንድነት ከአገልጋዮቿ ይጠበቃል። አንድ እረኛ ያላት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆንዋ መጠን በዚያ ስትመራ መቆየትዋን የሚያጸና በተግባር የተገለጠ አንድነት ተገቢ ነው።

ባጠቃላይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከአጥቢያ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ የምእመናንና የአባቶች ውስጣዊ አንድነት ላይ አጥብቃ መሥራት ነገ ልትጋፈጠው ካለው ፈተና ይጠብቃታልና ቁጭ ብሎ መወያየት መፍትሔ ላይ መድረስ አስፈላጊ ነው። ለዚህም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሆኑ ቅዱሳን አባቶቻችን ኃላፊነቱን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል።

# በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሥርዓተ ቀብር ላይ የተላለፈ የኀዘን መግለጫ

ክፍል አንድ

መጽሐፈ ሲራክ

## ዶ/ር ዐቢይ አህመድ

(የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር)

ብፁዕ አባታችን እንደ ጥሩ አባት ሩጫቸውን ጨርሰው ወደሚወዱት ወዳገለገሉት አባታቸው ሄደዋል፡፡ ከብፁዕ አባታችን ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘነው በዋሽንግተን ዲሲ ነበር፡፡ እሳቸው ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ ከሌሎች አባቶችና ወንድሞች ጋር በነበረው ውይይት መጠነኛ ክርክር ነበር፡፡ አይሄዱም ሌላ ጊዜ ይመጣሉ የሚል፡፡ ነገር ግን አባታችን ብዙ ሰው አይናገሩም ቢልም በወሳኝ ጊዜ ግን እጅግ ድንቅ ንግር እንደሚናገሩ ሰምቻለሁ፡፡ በመሆኑም ‹‹የመዳን ቀን ዛሬ ነው›› እናንተ ካልፈለጋችሁ አትሂዱ እኔ ግን ከልጄ ጋር እሄዳለሁ በማለት ነው ውሳኔያቸውን ያሳወቁን፡፡ ያ ውሳኔ ዛሬ እሳቸውን በክብር ለመሸኘት ብቻ ሳይሆን እንዲህ ሰብሰብ ብለን ታሪክ ያለን፤ ባህል ያለን፤ የራሳችን ዜማ ያለን መቀበል፣ ማሳደግ፣ መሸኘት የምንችልም ሕዝቦች መሆናችንን ለማሳየት ዕድል ስለሆኑን አባታችን ነፍሳቸውን በሰላም ከአባታቸው ጋር እንዲያኖርልን በድጋሚ ምኞቴን እገልጻለሁ፡፡

እዚህ በነበራቸው ቆይታ አልፎ አልፎ አባታችንን የመጎብኘት ዕድል አግኝቻለሁ፡፡ አባታችን እንደ እናንተ ሁሉ በእጅጉ በጸሎት ያግዙኝ ነበር፤ በእንባ ያግዙኝ ነበር፡፡ እንዲሁም በምክር ያግዙኝ ነበር፡፡ እሳቸውን ለማየት ስሄድ ቢያንስ ፍቅራቸውን በእንባቸው ይገልጹልኝ ነበር፡፡ አልፎ አልፎም ፈታኝ ነገር ሲገጥመን መቼም አባት አባት ነውና ቢሮ ድረስ እየመጡ ከወንድሞቻቸው ጋር በጽሑፍ ሐሳባቸውን፣ ጸሎታቸውን ፣ ምክራቸውን በተደጋጋሚ ገልጸውልኛል፡፡

ብፁዕ አባታችን ለእኔ እንደ እናንተው ሁሉ የመንፈስ፣ የጸሎት አባቴ ነበሩ፡፡ የዛሬው ኀዘን ልክ እንደ እናንተው የምጋራው እና አባቴን እንዳጣሁ የሚሰማኝ መሆኑን ልገልጽላችሁ ፈልጋለሁ፡፡ ብፁዕ አባታችን ዕድለኛ ናቸው፡፡ ዘመናቸውን በሙሉ የሚያምኑትን አምላክ እና የሚወዷትን ቤተ ክርስቲያን በታማኝነት አገልግለዋል፡፡ መናገር ሲገባቸው ተናግረው፣ መጸለይ ሲገባቸው ጸልየው መምከር ሲገባቸው መክረው በአርምሞና በጸጥታ መኖር ሲገባቸውም እንዲሁ በጸጥታ ኖረው በብዙ ያስተማሩን አባት ናቸው፡፡ አባታችን ወደሚወዱት አባታቸው ሄደዋል ነፍሳቸው በሰላም ከአባታቸው ጋር እንድትኖር እመኛለሁ አመሰግናለሁ፡፡



# ተቀዳሚ ሙፍቲ ሃጂ ኡመር እንድሪስ

## (የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚደንት)

እንኳን አባታችሁን በክብር ለመሸኘት አበቃችሁ፡፡ የሰውን ልጅ የሚያስከብረው፣ የሰውን ልጅ የሚያስወድደው፣ የሰውን ልጅ የሚያስፈልገው ሥራው ነው፤ ጥረቱ ነው፤ እውቀቱ ነው፤ እዝነቱ ነው፤ ሰው አስተማሪነቱ ነው፤ ሰው አስተነጋገዱ አቀባበሉ ነው፡፡ እሳቸው በተከበሩ ጠቅላይ ሚንስትር በዶ/ር ዐቢይ ምክንያት ከአሜሪካ የመጡ ዕለት የተናገርኩት አለ፡፡ የዚያን ዕለት ‹‹የኦርቶዶክስ አንድነት ዘላቂ እንዲሆን፤ ልባዊ እንዲሆን፣ እንዲሁም ውጫዊ እንዳይሆን መልእክት አስተላልፌ ነበር ይኸው ውጤቱ ዛሬ እየታየ ነው፡፡

የሰውን ልጅ የሚያስከብረው ፈጣሪ ጌታ ነው፡፡ የሰውን ልጅ ፈጣሪ ጌታ ነው የሚያስወድደው፡፡ የሰውን ልጅ አሸኛኘቱ፣ በሕይወቱ እንዲበጅለት የሚያደርገው ሲሞት የሚያስከብረው ፈጣሪ ጌታውና ልፋቱ፣ ጠባዩ፣ እዝነቱ ነው፡፡ ስለዚህ ዛሬ የእኚ አባት አሸኛኘት እየተገለጠ እያየን ነው፡፡ ከዚህ ለመመስከር የምንችለው የሰውን ልጅ ዕውቀት እንዴት አድርጎ እንደሚያከብረው የሰውን ልጅ መልካም ጠባይ እንዴት አድርጎ እንደሚያስከብረው የሰውን ልጅ መልካም ሥራ እንዴት አድርጎ እንደሚያስፈልገው ነው፡፡

በመጨረሻም ለማስተላለፍ የምፈልገው እሳቸው ሠርተዋል፤ ተምረዋል፤ አውቀዋል፤ ጳጳስ ደረጃ ለመድረስ እንዲህ በቀላል ደረጃ እሚደረስ እንዳልሆነ ሁላችሁም ታውቃላችሁ፤ ሁላችንም እናቀውቃለን፡፡ ስለዚህ እኔ የማስተላልፈው ከመንግሥት ጀምሮ የሃይማኖት አባቶች እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባጠቃላይ ክርስቲያኑም እስላሙም እንድንዋደድ፣ እንድንከባበር፣ ጠብን እንድንተው፣ ማፈናቀልን እንድንተው፣ ግድያን እንድንተው፣ ለሰላም ሁላችንም ዝግጁ እንድንሆን አደራ ለማለት እፈልጋለሁ፡፡

አባታችንም ከአባታቸው ጋር በሰላም ይገናኙ እላለሁ አመሰግናለሁ፡፡



# ካርዲናል ብርሃነ ኢየሱስ ሱራፌል

## (የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዚደንት)

በዛሬው ዕለት በዚህ የመስቀል አደባባይ የተሰበሰብነው ታላቅ አባት በማጣታችን እሳቸውን ለመሸኘት ነው፡፡ አባትን ማጣት ሁል ጊዜ ያሳዝናል፤ አባት ጥላ ነው፤ አባት ከለላ ነው፡፡ እንዲሁም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ እንደተናገሩት ይህ የኀዘን ቀን የመላው ኢትዮጵያ ኀዘን ነው፡፡ ስለዚህም ነው እኛ እዚህ ያለነው በመላው ኢትዮጵያ ያሉትም ወገኖቻችን እኒህን አባት በታላቅ ሃዘን የሚሸኙት፡፡

ሁል ጊዜ የምንሰማው እኚህ ታላቅ አባት ብዙ መከራ ያዩ፤ ስደት ያዩ ሆኖም ግን ሀገራቸውን ኢትዮጵያን የወደዱ፣ ያከበሩ፣ ለአንድነትም የቆሙ ስለሆነ ለእኛ ታላቅ ምሳሌ ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ ሲነገር እንደሰማነው እሳቸው ብዙ አይናገሩም ነበር ነገር ግን በአርምሞና በጸሎት ለእግዚአብሔር የሚያስፈልገውን ሁሉ ሲናገሩ በጾም በጸሎት ያሳለፉ ታላቅ አባት ነበሩ፡፡ አሁንም ወደሚወዳቸው ወደ አገለገሉት ወደ ጌታችን ወደ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሄዱ ‹አንተ ደግና ታማኝ አገልጋይ ና ወደተዘጋጀልህ ሥፍራ ግባ› በተባለው መሠረት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ወደ ዘለዓለማዊ ዕረፍት ነው የሄዱት፡፡ እኛም በሞታቸው ብናዝንም ወደ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደሚወዷት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ መላእክት ስለሄዱ የእኛ ጠበቃ በመሆን ስለ ኢትዮጵያ የሚናገሩት ብዙ ነገር አለ፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ መከራ ያየች በሰሜን በምዕራብ እንዲሁም አሁን ደግሞ በምሥራቅ በምናየው ድርቅ ሁሉ ብዙ ችግር እያየች ነውና እኚህ ደግ አባት የኛ ጠበቃ በመሆን በጌታ ቀኝ በመቀመጥ ኢትዮጵያ እንዳትረሳ ፣መከራዋ እንዲያልፍና በአንድነት ፣በፍቅር፣ በታሪክ የታወቀች ሀገራችን ተከብራ እንድትኖር ይጸልዩልናልና ብፁዕ አባታችን ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ፣ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት፣ ምእመናን በዚህ እንድትጽናኑ አደራ ለማለት እወዳለሁ፡፡
ነፍሳቸውን በጻድቃንና በመላእክት ዘንድ ያስቀምጥልኝ እላለሁ፡፡



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ፍራንሲስ

### (ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን ከሮም በኤምባሲው ዋና ጸሐፊ በኩል)

ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ



በቅዱስ አባታችን በአቡነ መርቆሬዎስ ኅልፈት ከባድ ኀዘን ተሰምቶኛል ስለዚህም ለእርስዎ ለቅዱስነትዎ፣ ለሊቃነ ጳጳሳቱ፣ ለካህናቱ፣ ለመነኮሳቱ ፣ለምእመናኑ ሁሉ ከልብ የመነጨ ኀዘኔን እየገለጽኩ ወንድማዊ ሰላምታዬን፤ በኀዘናችሁ ከእናንተ ጎን በወንድምነት መንፈስ መቆሜን ላረጋግጥላችሁ ፈልጋለሁ፡፡

በዚህ በኀዘናችሁ ጊዜ መላው ዓለም እናንተን ይመለከታል፡፡ በተለይ ክርስቲያኑ ዓለም ታላቅ አባት ጠንካራ መንፈሳዊ እረኛ፣ በጥበብ የተሞላ እረኛ፣ ሕዝቡን ባስቸጋሪ ጊዜ የመራ መልካም እረኛ፣ አጥቶአል እግዚአብሔር በመንግሥቱ፣ በቀኙ እንዲያኖራቸውና ነፍሳቸው የዘላለም ዕረፍት እንዲያገኝ እመኛለሁ፡፡

# የዓለም አብያተክርስቲያናት ኅብረት ጉባኤ፣ ጀኔቫ

አራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከዚህ ዓለም ድካም ማረፋቸውን የሰማነው በከፍተኛ ኀዘን ውስጥ ሆነን ነው፡፡ ስለሆነም የተሰማንን ጥልቅ ኀዘን እየገለጥን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ለሚኖሩ የእምነቱ ተከታዮች መጽናናትን እንመኛለን፡፡

ቅዱስነታቸው ለክርስትና ሕይወት ላበረከቱት አስተዋጽኦ ዕውቅና እንሰጣለን፡፡ በተለይ ከ፳፰ ዓመታት በላይ ለሁለት ተከፍላ የነበረችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወደ አንድ ለማምጣት ያደረጉት ጥረት የታላቅነትና የዕረቀ ሰላም ምልክት መሆናቸውን ያስመሰከሩበት ተግባር ነው፡፡

ነፍሳቸው በሰላም ትረፍ፤ በረከታቸው ይድረሰን!

oikoumene World Council of Churches

# ሞር ኢግኔሺየስ ኤፍሬም

### ከሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት

አራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከዚህ ዓለም ድካም ማረፋቸውን ከሰማንበት ጊዜ ጀምሮ በጣም አዝነናል፡፡ በጊዜ እጥረት ምክንያት በቅዱስነታቸው ሥርዓተ ቀብር ላይ የሚገኝ ተወካይ ባለመላካችን በጣም እናዝናለን፡፡ ነገር ግን የቅዱስነታቸው በረከት ካለንበት እንደማይለየን እናምናለን፤ እኅት ቤተ ክርስቲያንችንና ተከታዮቿንም ሁልጊዜ በጸሎት እናስባቸዋለን፡፡



በሶርያ ኦርቶዶክስ ቅዱስ ሲኖዶስ፣ አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ ካህናት አገልጋዮችና ምእመናን ስም በቅዱስነታቸው ዕረፍት ምክንያት የተሰማንን ጥልቅ ኀዘን እየገለጥን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ፣ ለአበው ሊቃነ ጳጳሳት እንዲሁም ለአገልጋዮችና ምእመናን መጽናናትን እንመኛለን፡፡

# በአገልግሎት ዘመናቸው ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ልዕልናና አንድነት ሲሠሩ ቆይተዋል

ካሳሁን ለምለሙ

የጸሎት አባት፣ሩኅሩኅ፣ ከአንደበታቸው ክፉ የማይወጣ፣ለመጥፎ ተግባር ያልተገዙ፣የመልካም ምግባር ምሳሌና የደግነት መለኪያ አባት ነበሩ፡፡ የሰውን ልጅ መከፋትና ማዘን የማይወዱ ለተቸገሩ አጋዥና ረዳት፣ የታመመን የሚጠይቁ፣ የተጣላን የሚያስታርቁ፣ ሰላምንና አንድነትን የሚሰብኩ እውነተኛ አገልጋይ አባት ነበሩ፡፡

በቤተ ክርስቲያን ከልጅነት እስከ ዕውቀት ባካበቱት ዕውቀት በደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን፣በደብረ ወገግ አሰቦት ሥላሴ አንድነት ገዳም፣ በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም፣በአዲስ ዓለም ማርያም አንድነት ገዳም፣እንዲሁም በደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም በአበምኔትነት በቅንነትና ፍጹም መንፈሳዊ በሆነ አባትነት አገልግለዋል፡፡ በአገልግሎት ዘመናቸው በአገልጋዮችና በምእመናን ዘንድ እጅግ ተወዳጅነትን ያተረፉ ከመሆናቸው የተነሣ በዝውውር ምክንያት ወደሌላ የአገልግሎት ቦታ ሲሄዱ እንኳን በተሰበረ ልብ ውስጥ ሆነው ነበር የሚዛወሩት፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ባገለገሉበት ዘመን ሁሉ ከምስጋናና ከአክብሮት ውጭ በአስተዳደራዊ ብቃታቸው በምእመናንም ሆነ በአገልጋዮች ዘንድ ምንም ዓይነት ቅሬታ ያልተሣባቸው ቅን አባት ነበሩ፡፡



አባ ገብረ ሕይወት

ከሰዎች ጋር ከነበራቸው አዎንታዊ ግንኙነት ባሻገር በተለያዩ ገዳማት በአገልግሎት በቆዩባቸው ጊዜያት ሁሉ በጾምና በጸሎት ተወስነው ከሥውራን አባቶች ጋር ይገናኙ ነበረ፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው የተማሩ ዕውቅ የቅዳሴ መምህር ነበሩ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ያስተማረቻቸውን ትምህርት በተግባር በመተርጎም ተዘዋውረው ባገለገሉባቸው በተለያዩ አካባቢዎች ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል፡፡

ትውልድ በምግባር እንዲቀና፣ በመንፈሳዊ ትምህርትም እንዲበቃ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል፡፡ ብዙዎችን ከኃጢአት ወደንስሓ፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን እንዲመለሱ አድርገዋል፡፡ ሰፊውን የአገልግሎት ዘመናቸውን በቅዳሴና በስብከተ ወንጌል አገልግሎት አሳልፈዋል፡፡ ልማትና የተፈጥሮ ሀብት ክብካቤ ላይም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ሠርተዋል፡፡ በአገልግሎት ዘመናቸው ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን እንጅ ለእኔ ሳይሉ ለቤተ ክርስቲያን ልዕልናና አንድነት ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ራሳቸውንም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው የሰጡ እውነተኛ ነበሩ፡፡ የዛሬው የቤተ አብርሃም እንግዳችን ክቡር ንቡረ ዕድ አባ ገብረ ሕይወት መልሴ ሲሆኑ አባታችን ከረጅም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዘመን በኋላ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በተወለዱ በዘጠና ሁለት ዓመታቸው ኅዳር ፳፪ ቀን ፳፻፲፬ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ዝግጅት ክፍላችንም ከሕይወት ታሪካቸው ተነሥቶ የትምህርትና የአገልግሎት ዘመናቸውን የሚመለከት ጽሑፍ ይዞ ቀርቧል፤ መልካም ንባብ፡፡

አባ ገብረ ሕይወት መልሴ በቀድሞው ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በወራና ወረዳ ወንበሮ ኪዳነ ምሕረት ከአባታቸው ከቀሲስ መልሴ ጨፍቅና ከእናታቸው ወ/ሮ አበባሽ ወርቅ ኃይለ መስቀል ኅዳር ፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ.ም ተወለዱ፡፡ አባ ገብረ ሕይወት ከልጅነታቸው ጀምሮ ከቤተሰቦቻቸው ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የቅርብ ክትትል ይደረግላቸው የነበረ በመሆኑ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከ፲፱፻፳፱ እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ከወላጅ አባታቸው እግር ሥር ተቀምጠው ንባብ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ሰዓታትና ግብረ ዲቁና ጠንቅቀው ተምረዋል፡፡ በመቀጠልም ፲፱፻፵ ዓ.ም ጀምሮ ከቤተሰቦቻቸው የመኖሪያ አካባቢ በቅርብ ርቀት በሚገኘው ዶቃቂት ደብረ ኃይል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከየኔታ እስጢፋኖስ የዜማ፤ በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ደግሞ ከየኔታ መንገሻ የአቋቋም ትምህርት ተምረዋል፡፡

የኔታ መንገሻ ከብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ ጋር ወደ አሰቦት ገዳም ተዛውረው በሄዱበት ወቅትም ወደ አሰቦት ገዳም በመሄድ የጾዋትወ ዜማ፣ አቋቋምና ዝማሬ መዋሥዕት ትምህርትን ከ፲፱፻፵፩ እስከ ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ድረስ ተምረዋል፡፡ በወቅቱ በነበረው የአሰቦት አንድነት ገዳም ሥርዓት መሠረትም የካቲት ፳፯ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ.ም በአባ ዮሐንስ ያዕቆብ አባትነት ሥርዓተ ምንኵስናን ተቀብለዋል፡፡ ማዕርገ ምንኵስናን ከተቀበሉ በኋላም ሌሎች መነኮሳት በተግባረዕድ ገብተው ሲሰማሩ አባ ገብረ ሕይወት መልሴ ግን ከየኔታ እስጢፋኖስ ዘንድ

ተመድበው ቀለም በጥብጠው ብራና ዳምጠው በቁም ጽሕፈት አንድ ድጓና ዝማሬ መዋሥዕት ጽፈው ለአሰቦት ገዳም አስረክበዋል፡፡

አባ ገብረ ሕይወት መልሴ በዲቁና እያገለገሉ ቆይተው በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ማዕርገ ቅስና ተቀብለው በነበራቸው መልካም ሥነ ምግባርና የሙያ ብቃት በገዳሙ በመጋቢነት ተመድበው እስከ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም ድረስ በታታሪነት ቤተ ክርስቲያናቸውን አገልግለዋል፡፡ በገዳሙ በመጋቢነት ሥራ እየተጉ የነበሩት አባት ለትምህርት ካላቸው ጽኑ ፍላጎት የተነሣ የመጋቢነት ኃላፊነታቸውን በማስረከብ የኤታ መንገሻ ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ እርሳቸውን ተከትለው ተመልሰው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ከመምህር ወርቅነህ መዝገበ ዘንድ ቅዳሴና የሐዲሳት ትርጓሜ መጻሕፍት ተምረዋል፡፡ በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም በመልአከ ሰላም ሳሙኤል (የእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና የኮሌጁ መምህር) ጋባዥነት የተሰጠውን የመግቢያ ፈተና በማለፍ የመጀመሪያው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪ በመሆን እስከ ፲፱፻፶፬ ዓ.ም ድረስ ለሦስት ዓመት የትምህርተ ሃይማኖት (የቴኦሎጂ) ትምህርታቸውን በመከታተል ከዓፄ ኃይለ ሥላሴ እጅ ዲፕሎማ ተቀብለዋል፡፡

አባ ገብረ ሕይወት ዲፕሎማቸውን ከያዙ በኂላ ከታኅሣሥ ፲፱፻፶፬ ዓ.ም ጀምሮ በቀድሞው ይፋትና ጥሙጋ አውራጃ በተባለ ቦታ በሊቀ ካህንነት ተሹመዋል፡፡ በወንጌል አገልግሎታቸውም ብዙዎችን አሳምነው አጥምቀው የሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡ በወቅቱ ጠንካራ የስብከተ ወንጌል ኮሚቴ ማቋቋም አስፈላጊ ስለነበር ከመንፈሳዊ ኮሌጅ ከተመረቁት ተማሪዎች መካከል ፈተና በመስጠት በተገኘው ውጤት መሠረት ክቡር ንቡረዕድ አባ ገብረ ሕይወት ፀሐፊ ሆነው አገልግለዋል፡፡

ንቡረ ዕድ አባ ገብረ ሕይወት ከ፲፱፻፶፭ እስከ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የድርሰትና ስብከተ ወንጌል አገልግሎት ሥራ አስኪያጅነት ተመድበው አገልግለዋል፡፡ በወቅቱ ይታተሙ በነበሩት ዜና ቤተ ክርስቲያንና የተክለ ሃይማኖት ጋዜጦች ላይም በሥነ ጽሑፍ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡ ከዜና ቤተ ክርስቲያን ጎን ለጎን በማስታወቂያ ሚኒስቴር የሚዘጋጀው ዜና ከመነበቡ በፊትም እርሳቸው ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ ለመላው ኢትዮጵያ ይተላለፍ ነበር፡፡ በ፲፱፻፶፭ዓ.ም በጠቅላይ ቤተ ክህነት የድርሰትና የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ኃላፊ በመሆን በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ የሚተላለፈውን የወንጌል ስብከትና የዝማሬ አገልግሎት አስተባብረዋል፡፡ ይህንን ጥረታቸውን የተረዱት የቅዱስ ፓትርያርኩ እንደራሴ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስም በቤተ ክህነት ከነበራቸው ኃላፊነት በተጨማሪ ከሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ.ም ጀምሮ የደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው እንዲሠሩ ሹመዋቸዋል፡፡

ከዚያም ከ፲፱፻፶፰ እስከ ፲፱፻፸ ዓ.ም በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት ላይ በነበሩበት ወቅት የቤተ ክርስቲያኑ ዐውደ ምሕረት እንዲጸዳና እንዲስተካከል ለአገልግሎትም ምቹ እንዲሆን አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያኑን ሰንበት ትምህርት ቤት አጠናክረዋል፡፡ አሁን በአገልግሎት ላይ ያለውን የስብከተ ወንጌል አዳራሽም አሠርተዋል፡፡

በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም እንዲሁ ወደ ደብረ ወገግ አሰቦት ሥላሴ አንድነት ገዳም ተዛውረው ነበርና በተዛወሩበት ወቅት ሳያጠናቅቋቸው የቀሯቸውን ሥራዎች ለማጠናቀቅ በድጋሜ ደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያንን እንዲያስተዳድሩ መመደባቸው መልካም እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ በወቅቱ ሦስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል፡፡ የአብነት ትምህርት ቤቱንም በሚገባ አጠናክረዋል፤ በአስኳላው ትምህርትም ከአንድ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ዘመናዊ ትምህርት ቤት አስገንብተዋል፡፡ ከ፲፱፻፸፯ እስከ ፲፱፻፹ ዓ.ም ታአካ ነገሥት በዕታ ለማርያም ገዳምንም ደርበው በፍቅርና በአንድነት አስተዳድረዋል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት ገዳሙ ከፍተኛ ፈውስ እየሰጠ ያለውን ጸበል ቤት እንዲቋቋም ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ጉዳይም የዘወትር አጀንዳቸው በመሆኑ በዚህ ዙሪያም ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ ሙዚየም በማስተማሪያነት ሊያገለግል በሚችል መልኩ ተደራጅቶ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርገዋል፡፡ የአቡነ ፊሊጶስን ቤተ ክርስቲያንም ካሳነጹ በኂላ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ረዥም ጊዜ የጸለዩበትና አጽማቸው የነበረበት ቦታ ደብረ አሰቦ ላይ ደግሞ ጸሎት ቤት አሠርተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽርሐ ጽዮን ጎል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከ፲፱፻፸፯ እስከ ፲፱፻፹ ዓ.ም የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ለማጠናከርና የመንግሥተ ሰማያት ወራሾችን ለማብዛት የሚያደርጉት ጥረት አካል የሆነ የሠራተኞች ጉባኤ እንዲመሠረትና መርሐ ግብሩም በየሳምንቱ ዐርብ እንዲካሄድ አድርገዋል፡፡ የጸበል ቤትም አሠርተዋል፤ ቤተ ክርስቲያኑንም አሳድሰዋል፡፡ በተጨማሪም በጠቅላይ ቤተ ክህነት የመንፈሳዊ ፍርድ ቤት አባል ሆነው አገልግለዋል፡፡ ከ፲፱፻፹ እስከ ፳፻፰ ዓ.ም በርዕሰ አድባራት ወገዳማት አዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ማርያም የተቃጠለውን ሙዚየምና ቤተ መንግሥት የቀድሞ ይዘቱን ሳይለቅ ተመልሶ እንዲሠራ አድርገዋል፡፡ ተዳክሞ የነበረውን የአብነት ትምህርት ቤትም አጠናክረው ከሦስት ሺህ በላይ ሊቃውንትን እንዲያፈራ አድርገዋል፡፡ ገዳሙም በውጭና በሀገር ውስጥ እንዲታወቅ የማስተዋወቅ ሥራ ሠርተዋል፡፡

የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በገጠርና በከተማ እንዲስፋፋ ለማድረግም በርካታ ደቀ መዛሙርትን ወደ ተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ማሠልጠኛዎች ልከው በማስተማር ሰባክያነ ወንጌልና የአብነት መምህራንን አፍርተዋል፡፡ የአዲስ ዓለም ማርያም ገዳም የተመሠረተበትን መቶኛ ዓመት በ፲፱፻፺፬ ዓ.ም በድምቀት እንዲከበር አድርገዋል፡፡

ጊዜያዊና ቋሚ የገቢ ምንጮችን በማፈላለግ የደብረ ተዋሕዶ ቅዱስ ሚካኤል ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን አሳድሰዋል፡፡ በኤጄሬ ወረዳ በማረሚያ ቤት ለሚገኙ የሕግ ታራሚዎችና አባሎች አገልግሎት የሚሰጥ የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን አሳንጸው ለአገልግሎት አብቅተዋል፡፡ የርዕሰ አድባራት ወገዳማት አዲስ ዓለም ማርያም ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ መቃኞ ቤትን አሳድሰው አገልግሎት

እየሰጠ ይገኛል፡፡ ዘመናዊ የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት ቤትም አስገንብተዋል፡፡

የጥምቀተ ባሕር ቦታ የቤተ ክርስቲያኗ ይዞታ ሆኖ እንዲከበር አድርገዋል፡፡ የችግኝ ተከላና እንክብካቤ በየዓመቱ በዕቅድ ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡ በተለምዶ ማርያም ምንጭ እየተባለ በሚጠራው ቦታ ላይ በእመቤታችን ስም በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ፈውሶች እየሰጠ የሚገኘውን ጸበል ቦታ ከጥንቱ በተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርገዋል፡፡ ከአዲስ አበባ ወደ ወሊጋ ከሚወስደው የአስፋልት መንገድ ተገንጥሎ እስከ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚዘልቀውን መንገድ በአስፋልት እንዲሸፈን አሠርተዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያኗን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አሠርተው በ፳፻፮ ዓ.ም ተረክበዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ ግቢ በጎርፍ እንዳይሸረሸር የባዞላ ንጣፍ አሠርተዋል፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የክርስትና ቤት፣ ሁለት መለስተኛ አዳራሾችና ለጽ/ቤት የሚያገለግሉ ቢሮዎችን የያዘ ሕንጻም አሠርተዋል፡፡ ለአንድ መቶ ሃያ ተረጂዎች የሚሆን የአረጋውያን መርጃ ፕሮጀክት ለማቋቋም ዐሥር ሄክታል መሬት ከመንግሥት ተረክበዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በሣር አምባ ደብረ ገነት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም ከአራት ሚሊዮን ብር በላይ ወጭ የፈጀ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል፡፡ በቤተ ክርስቲያኑም ግቢ ውስጥ አሥራ አንድ ምሰሶች አስተክለው የኤሌክትሪክ መብራት አስገብተዋል፡፡ ከዐሥር ሄክታር በላይ የሆነ መሬት ካርታ አሠርተው ለገዳሙ ገቢ አድርገዋል፡፡ የቤተሰቦቻቸውን መሬት ጭምር ለገዳሙ አገልግሎት እንዲውል አበርክተዋል፡፡ እንዲሁም ለገዳሙ አገልግሎት የሚውሉ ሦስት ወፍጮዎችን አስተክለዋል፡፡

በገዳሙ የሀገር በቀል ዛፍ በስፋት እንዲለማ አድርገዋል፡፡ ገዳሙን የንጹሕ ውሃ መጠጥ ተጠቃሚ አድርገዋል፡፡ የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መፍለቂያ የሆነ የአብነት ትምህርት ቤት እንዲቋቋም አድርገዋል፡፡ ተከታታይ ሥልጠናዎችን ለካህናት በመስጠት በስፋት የስብከተ ወንጌል አገልግሎትና ሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ አድርገዋል፡፡ በደብሩ የሚገኙትን ደቀ መዛሙርት በልዩ ልዩ ተግባረ ዕድ በሠለጠኑ አስተማሪዎች እንዲሠለጥኑ አድርገዋል፡፡ በሀገረ አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚቴ በማቋቋም የአብነት ትምህርት ቤት እንዲጠናከር ለምታደርገው አስተዋጽኦ ክፍተኛ የሆነ አባታዊ እገዛ አድርገዋል፡፡ ዕድሜ ጠገብ የሆነችውን የኮሽም ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንን አሳድሰዋል፡፡ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም አምላካዊ ተአምራት የተፈጸመባቸውን ቅዱሳት መካናትን በመጎብኘት የተለያዩ ድጋፎችንም አበርክተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ለሕንጻ የሚሆን ምቹ ቦታ ገዝተው የቅዱስ ፊልጶስን ቤተ ክርስቲያን ተክለዋል፡፡ የጻድቁ አቡነ ጎርጎርዮስን ታቦት አስገብተው ከቦሌ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጋር በአንድነት እየተገለገለ ይገኛል፡፡ በግል ገንዘባቸው ቦታ ገዝተውም ገዳመ ኢየሱስን ተክለዋል፡፡ በደብረ ብርሃን በአንሳስ ማርያም እንዲሁ ትምህርት ቤት አሠርተዋል፡፡ በሆለታ ከተማ የእርሻ ምርምር ጣቢያ ውስጥ በታነጸው አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ግንባታ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ክርስትና የተነሡባትን የወንበሮ ቅድስት ኪዳነ ምሕረትን ቤተ ክርስቲያንም አሳድሰዋል፡፡ ከዋናው መንገድ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ ድረስ የሚሆን የመኪና መንገድ አሠርተዋል፡፡ አባታችን "አቅሜ ደከመ ከእንግዲህ ይበቃኛል፣ ልረፍ" እንኳን ሳይሉ ጤና ባጡበትና እርጅና በተጫናቸው ሰዓት በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት የምትገኘዋን የጥንታዊትና ታሪካዊቷን ደብረ ዕንቍ አሰግድመኝ ቅድስት ድንግል ማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ድንቅ በሆነ ሁኔታ አስገንብተው ግንቦት ፲፰ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም አስመርቀዋል፡፡ በእርጅና ዕድሜያቸው ጭምር የአብነት ትምህርት ቤቶች እንዲጠበቁና ተሻሽለው እንዲቀጥሉ በመላው ዓለም በመዞር የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ለማሰባሰብ ተግተዋል በዕድሜና በጤና እክል ምክንያት ከመደበኛ አገልግሎታቸው በጡረታ ቢገለሉም በድካመ ሥጋ እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ በአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ ያደርጉት የነበረውን አገልግሎት አላቋረጡም ነበር፡፡በተለይም የርዕሰ አድባራት ወገዳማት አዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ማርያምን የተክሌ አቋቋምና የአንኮበር ወረብ ሊቃውንት መፍቂያ የማድረግ ሐሳብ ነበራቸው፡፡ በዚህም ሥራቸው የዳንኤል እይታዎች የ፳፻፲፫ ዓ.ም የበጎ ሰው ተሸላሚ አድርጓቸዋል፡፡ ንቡረ ዕድ አባ ገብረ ሕይወት መልሴ በሕይወት ዘመናቸው ላበረከቱት ከፍተኛ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ልዩ ልዩ ሜዳልያዎች፣ የምስክር ወረቀቶችና ሽልማቶች ተበርክተውላቸዋል፡፡

ክቡር ንቡረ ዕድ አባ ገብረ ሕይወት መልሴ ከልጅነት እስከ ዕውቀት እንዲሁም ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ትጋታቸው ለሌሎች አገልጋዮችም ሆነ ለዚህ ዘመን ትውልድ ከአዕምሮ የማይጠፋ ከሕሊና የማይሰወር ትምህርት አስተምረው አልፈዋል፡፡ እኛ የዚህ ዘመን ትውልድም የእርሳቸውን የአገልጋይነት መንፈስ ተረድተን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንና ሀገራችንን ፍጹም በሆነ ቅንነት ልናገለግል ይገባል፡፡ በቅንነትና በታማኝነት ማገልገላችን እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ይሆናል፡፡

የአባ ገብረ ሕይወት መልሴ የአገልግሎት ሕይወት ብዙዎቻችንን ለአገልግሎት እንድንተጋ ከማገዙ ባሻገር በውስጣችን መንፈሳዊ ቅናትና ቁጭት የሚፈጥርብን ነው፡፡ አገልጋይነት የሚኖረው ውስጣዊ ርካታ በምንም የማይሰፈር ማይለካ ነውና ማንኛችንም ብንሆን በየተሰማራንበት የሙያ መስክ ሁሉ የአገልጋይነት ስሜት ሊኖረን ይገባል፡፡ በተለይ እኛ ምእመናን ቤተ ክርስቲያናችንን ፍጹም በሆነ የአገልጋይነት ስሜት ካገለገልን ቤተ ክርስቲያናችን ያሉባትን ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች በቀላሉ መሻገር ትችላለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን እስከ አስተምህሮዋ ከትውልድ ወደ ትወልድ እንድትሻገር ሁላችንም በአገልጋይነት መንፈስ በትጋትና በቅንነት ልናገለግላት ያስፈልጋል፡፡

አባታችን በቅንነትና በታማኝነት ለበርካታ ዘመናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ቆይተው ኅዳር ፳፪ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ቀብራቸውም ኅዳር ፳፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ፲፱ ዓመት በቅንነትና በፍጹም መንፈሳዊ አባትነት ባገለገሉባት በጥንታዊቷና ታሪካዊቷ በርዕሰ አድባራት ወገዳማት አዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመ ሲሆን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ አያሌ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ዘመድ ወዳጆቻቸው፣ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውና የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ተገኝተዋል፡፡ ነፍሳቸውን በደጋጎቹ አባቶቻችን በአብርሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ አጠገብ ያሳርፍልን፤ የአባታችን በረከታቸው ይድረሰን፡፡ አሜን፡፡

# “ብፁዓን አባቶች በሚሰጡት ምክርና አቅጣጫ መሠረት በሀገረ ስብከቱ በርካታ የነፍስ አድን ሥራዎች ተሠርተዋል”

ካሳሁን ለምለሙ

ጦርነቱን ተከትሎ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ባቋቋሙት የሰላም ግብረ ኃይል አባል በመሆን በርካታ በጎ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡ ከብፁዕነታቸው ጋር በመሆን የከፋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችን አጽናንተዋል፤ የራበውን አጉርሰዋል፤ የታረዘውን አልብሰዋል፡፡ የሀገረ ስብከቱ ሰላምና ደኅንነት እንዲጠበቅ የጎላ ድረሻም ነበራቸው፤ አብያተ ክርስቲያናት፣ የመንግሥትና የግል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከባድ ጉዳትና ዝርፊያ እንዳይፈጸምባቸው ጥረት ሲያደረጉ ቆይተዋል፡፡

ምእመናን ለከፋ ጥቃት፣ስደትና እንግልት እንዳይዳረጉ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር በጋራ እግዚአብሔር የሚወደውን በሰውም ልብ ውስጥ የሚኖረውን የነፍስ አድን ሥራ ሲሰሩ ቆይዋል፡፡ ይህንን ሁሉ ተግባር በዚያ የጭንቅ ዘመን ሲከውኑ የነበሩት ደግሞ የሰሜን ውሎ ሀገረ ስብከት የሰላም ግብረ ኃይል አባል አድርጎ የመደባቸው መምህር ለይኩን ብርሃኑ ናቸው፡፡ ዲያቆን አሻግሬ አምጤ በወልዲያ ከተማ (የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት መቀመጫ) ተገኝቶ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ስለነበረው ጉዳይ ከእርሳቸው ጋር ያደረገውን አጭር ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጦርነቱ ወቅት ምእመናንን ከማጽናናት አንጻር የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ብፁዓን አባቶች ድርሻ ምን ነበር?**

**መምህር ለይኩን ብርሃኑ፡-**የጦርነት የመጀመሪያው ባሕርይ አውዳሚነት ነው፡፡ ጦርነት ሕዝብ ይጨርሳል፤ ንብረት ያወድማል እንዲሁም የሕዝብን ሥነ ልቡና ይጎዳል፡፡ በሀገራችን በተለይም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከተሰው ጦርነት ምክንያት በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከትና አካባቢው የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቀው ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን አካባቢውን ለቆ እንዳይሰደድና ለከፋ አካላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት እንዳይጋለጥ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቃነ ጳጳሳት የሆኑት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስና ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል፡፡ ሁለቱ ብፁዓን አባቶች የአካባቢው ማኅበረሰብ በርኃብና በሕክምና እጦት እንዳይሞት ገንዘብ ከባለፀጎች እየተበደሩ የተራበውን ሲመግቡ ቆይተዋል፡፡

በተቻለ መጠን የሕክምናና የመድኃይኒት አቅርቦት እንዲያገኙም ጥረት አድርገዋል፡፡ የተፈጥሮ ሀብቶች ፣የግለሰብና የመንግሥት ተቋማት ጨርሰው እንዳይወድሙና እንዳይዘረፉ እንዲሁም ገዳማትና ድባራት ጉዳት እንዳይደርስባቸው ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ የሰላምና የፀጥታ ግብረ ኃይል በማዋቀርም በአካባቢው ጦርነት ከተከሰተበት ጊዜ አንሥቶ የአካባቢው ሰላም በአንፃራዊነት እንዲጠበቅ አድርገዋል፡፡

ብፁዓን አባቶች ሕዝበ ክርስቲያኑን በተከታታይ ወንጌል በማስተማራቸውና በማፅናናታቸው ሕዝቡ ከስደትና ከከፋ ችግር ተጠብቆ ቆይቷል፡፡ በአጠቃላይ ብፁዓን አባቶች በሚሰጡት ምክርና አቅጣጫ መሠረት በሀገረ ስብከቱ በርካታ የነፍስ አድን ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህም የተነሣ ችግሮችን በጋራ አልፈን እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ በሀገረ ስብከታቸው ተወስነው መቆየታቸው ይፈጠሩ የነበሩ ችግሮችን ከመቀነስ አንፃር ምን ድርሻ ነበረው?**

**መምህር ላይኩን፡-** ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ከጦርነቱ በፊት ከሀገረ



መምህር ለይኩን ብርሃኑ

ስብከታቸው ለተወሰነ ጊዜ ርቀው በአገልግሎት የሚቆዩበት አጋጣሚ ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ጦርነቱ ብዙም ሳይቆይ በመጀመሩ ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅና ምእመናንን ለማጽናናት በሀገረ ስብከታቸው መቆየትን መርጠዋል፡፡ እርሳቸው በሀገረ ስብከታቸው ተወስነው መቆየታቸው እኔን

ጨምሮ በርካታ ምእመናንና አገልጋዮች በአገልግሎታቸው እንዲቆዩና አካባቢያቸውን ትተው እንዳይሰደዱ አድርጓል፡፡ ምእመናን ከእግዚአብሔር በታች እርሳቸውን መጽናኛ አድርገው በአካባቢያቸው ፀንተው ቆይተዋል፡፡ ብፁዕነታቸው ምእመናን እንዲበረቱ፣ እንዲጽናኑና የጦርነቱ ሰለባ እንዳይሆኑ ጠንክረው ሲሰብኩ ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህም የተነሣ አብዛኛው አገልጋይና ምእመናን ተፅናንተው በአካባቢያቸው ተወስነው የቆዩ ሲሆን በአካባቢያቸው የሚፈጠሩ ችግሮች ሲኖሩም ከብፁዕነታቸውና እርሳቸው ካቋቋሙት የሰላምና ፀጥታ ግብረ ኃይል ጋር በመመካከር ሲፈቱ ቆይተዋል፡፡

በተለይ ብፁዕነታቸው በመንበራቸው ቆይተው ሕዝበ ክርስቲያኑን ባያፅናኑና ባያስተምሩ ኖሮ በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ እልቂት ይፈጠር ነበር፡፡ ከተሞችንና የተለያዩ የእምነትና የመንግሥት ተቋማት ጭምር አሁን ባሉበት ደረጃ አይገኙም ነበር፡፡ ከብፁዕነታቸው ጋር የነበሩ አገልጋዮች ሁሉ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የምእመናንን ሁለንተናዊ ችግር ለመቅረፍ ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩ ናቸው፡፡

> **ችግሮቻችንንም በደንብ እንድናይ አድርጎናል፤ እንዲሁም ከሌሎች እምነት ተከታይ ወገኖች ጋር መልካም የሆነ መስተጋብር እንዲኖረኝ ረድቶኛል። በችግሩ ምክንያት የሰው ልጅ ኑሮ በቅንጦትና በቴክኖሎጂ ብቻ ተንጠልጥሎ መኖሩ ችግር በመጣ ጊዜ ሕይወቱን የከፋ እንደሚያደርገው ጦርነቱ አስተምሮኛል።**

አካባቢው በታጣቂዎች ቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ ሁሉም የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎት አቁመው ስለነበር የአካባቢው ማኅበረሰብ ወልዲያ ከተማ ላይ እህል አስፈጭቶ የሚበላበት ሁኔታ ስላልነበረ በርካታ ኪሎሜትሮችን እህሉን በግመል እየጫነ የሚያስፈጭበት ሁኔታ መኖሩን የተመለከቱት ብፁዕነታቸው ኅብረተሰቡ የወፍጮ አገልግሎት በአካባቢው እንዲኖር አስችለዋል፡፡ በዚህ መሠረት ማኅበረሰቡ አስፈጭቶ መብላት ጀመረ፡፡ ወፍጮዎቹ አገልግሎት እንዲሰጡ የመንግሥትና የግለሰብ ጀኔሬተሮችን መጠቀም ተችሏል፡፡ የነዳጅ እጥረት በመኖሩም በውድ ዋጋ እየተገዛ ጭምር ወፍጮዎቹ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ሰዎች እህል በሚያስፈጩበት ወቅት ካላቸው ቀንሰው ለሌላቸው እንዲያካፍሉ ብፁዕነታቸው መመሪያ በሰጡት መሠረት ብዙ ሰዎችን መርዳት ተችሏል፡፡

በዚህ ሁኔታ ያን ክፉ ጊዜ በመረዳዳትና በመተጋገዝ ለማለፍ ተችሏል፡፡ ብፁዕነታቸው ላጡና ለተቸገሩ ወገኖች በየቤታቸው እየሄዱ እህልና ምግብ የማከፋፈል ሥራም ሠርተዋል፡፡ በወሊድና በእርግዝና ምክንያት የተቸገሩ እናቶችንንና በበሽታ ምክንያት በአልጋ ቁራኛ ለወደቁ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ልዩ ትኩረት ሰጥተው ያላቸውን ሀብት ሁሉ አሟጠው ተጠቅመዋል፡፡ ፊኖ ዱቄት ጨምሮ ሌላ የዱቄት ዓይነቶችን ቤት ለቤት በመዞር የማከፋፈል ሥራ ሲሠሩ ከመቆየታቸው በተጨማሪ ለእህል ወፍጮ ሠራተኞችና ለሕክምና ባለሙያዎች የማበርታቻ የገንዘብ ሽልማት አበርክተዋል፡፡

ብፁዕነታቸው የግላቸውና  የቤተ ክርስቲያን ሀብት ተሟጦ ካለቀ በኋላም በሀገረ ስብከታቸው ሥር ያሉ አጥቢያዎች ሁሉ ካላቸው ቀንሰው የተቸገሩ ወገኖችን እንዲረዱ አባታዊ መመሪያ በሰጡበት ወቅት በርካታ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የአቅማቸውን ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አብያተ ክርስቲያናቱም ሆኑ ብፁዕነታቸው ከግለሰቦችና ከድርጅቶች ሳይቀር ገንዘብ፣ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሶችን ተበድረው ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ያደርሱ ነበር፡፡

በዚህም የተነሣ በወልዲያና ዙሪያው የሚገኙ አጥቢያዎች ከግለሰቦችና ድርጅቶች ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ ብድር ወስደዋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአካባቢው አርሶ አደሮች ከአመረቱት ምርት ከአንድ ጣሳ ጀምረው አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ብፁዕነታቸው መመሪያ አስተላልፈው አርሶ አደሩም የተቻላቸውን ሁሉ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ ብፁዕነታቸውና ሌሎች አገልጋዮች በሀገረ ስብከታቸው መቆየታቸው የምእመናንን ስደት ቀንሷል፤ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳት አስቀርቷል፤የተቋማትንና የሰው ጉዳትን አስቀርቷል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጦርነቱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ችግር ውስጥ በወደቁበት ወቅት አካባቢዎን ጥለው ሳይሰደዱ በሕዝብ አገልጋይነትዎ መቀጠልዎ የፈጠረበዎት ስሜት ምንድን ነው? ከችግሩስ ምን ተማሩ?**

**መምህር ለይኩን፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ለስደት ሳልዳረግ በአካባቢዬ ቆይቼ የተቸገሩትን እንዳግዝ ያደረገኝን እግዚአብሔር አመሰግናለሁ፡፡ የተቸገሩና የከፋቸው ወገኖችን ረድቼ መጽናናትንና መጠገናቸውን ስመለከት ደግሞ የተለየ ልባዊ ደስታ

ፌጥሮልኛል፡፡ እንደእኔ እምነት የተቸገረን ሰው የመረዳትና የማጽናናት ያህል ደስታ የሚፈጥር በጎ ሥራ የለም፡፡ በዚህ መሠረት ለብዙ የተቸገሩ ሰዎች በችግራቸው ጊዜ ደርሰናል፡፡

ችግር ብልሀትን ያስተምራልና በችግራችን ወቅት ብዙ ብልሀቶችን እንድንማር ሆነናል፡፡ በግለሰብ ደረጃም ከብፁዕነታቸው ጎን ሆኜ በመማሬና በአለኝ አቅም እገዛ ማድረጌ ሕይወቴ ውስጥ ለውጥ አምጥቷል፡፡ ችግሮቻችንንም በደንብ እንድናይ አድርጎናል፤ እንዲሁም ከሌሎች እምነት ተከታይ ወገኖች ጋር መልካም የሆነ መስተጋብር እንዲኖረኝ ረድቶኛል፡፡ በችግሩ ምክንያት የሰው ልጅ ኑሮ በቅንጦትና በቴክኖሎጂ ብቻ ተንጠልጥሎ መኖሩ ችግር በመጣ ጊዜ ሕይወቱን የከፋ እንደሚያደርገው ጦርነቱ አስተምሮኛል፡፡ በዚህ መሠረት እኛ ኢትዮጵያውያን ያለን ፀጋ ብዙ እንደሆነ እንድረዳ አድርጎኛል፡፡

## ብፁዕነታቸው በመንበራቸው ቆይተው ሕዝበ ክርስቲያኑን ባያፅናኑና ባያስተምሩ ኖሮ በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ እልቂት ይፈጠር ነበር፡፡ ከተሞችንና የተለያዩ የእምነትና የመንግሥት ተቋማት ጭምር አሁን ባሉበት ደረጃ አይገኙም ነበር፡፡

ዘመናዊ የእህል ወፍጮ በማይኖርበት ጊዜ ሁሉም ሰው የድንጋይ ወፍጮን የመጠቀም ልምድ ቢኖረው እህሉን ፈጭቶ ተመግቦ ማደር እንደሚችል ተገንዝቢያለሁ፡፡ የድሮ ልማዶቻችንን ሳንጥል አዳዲስና የሚጠቀሙንን ልማዶች መተግበር እንችላለን፡፡ ክፉ ዘመን በመጣ ወቅት ተባብሮና ተጋግዞ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን የጦርነቱ ጊዜው ትልቅ ትምህርት ሰጥቶ አልፏል ያለው ለሌለው አካፍሎ ቢኖር በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ የሚወደድ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም ባደረግነው ጠንካራ የመረዳዳት ሥራ አንድም ሰው በርሃብ አልሞተብንም፡፡ ይህ ሥራ በግሌ ሁሌም ሲያኮራኝና ውስጣዊ የደስታ ስሜት ሲፈጥርብኝ ይኖራል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በወቅቱ የነበረውን የክርስቲያኖች ንቃተ ኅሊናና ወደ ቤተ ክርስቲያን የመቅረብ ፍላጎት እንዴት ይገለፃል?**

**መምህር ለይኩን ብርሃኑ፡-** ብፁዕ አባታችን አቡነ ኤርምያስ ከሐምሌ ወር ፳፻፲፫ ዓ/ም ጀምሮ ጸሎተ ምሕላ ካወጁ በኋላ አብዛኛው ምእመን የጸሎት መርሐ ግብሩን ሳያስታጉል ተገኝቷል፡፡ ብፁዕነታቸው በሕመም ላይ ሆነውም ቢሆን ጸሎተ ምሕላው ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ምእመናንን ሲያጽናኑና ሲደግፉ ቆይተዋል፡፡ በዚህ የተነሣ የብፁዕነታቸውን ድምጽ የሰሙ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ቅጥር የማይርቁበትና አታድርጉ የተባሉትን ነገር ሁሉ የማያደርጉበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቆይቷል፡፡

ምእመናን የራሳቸው ያልሆነ ነገር እንዳይነኩ ብፁዕነታቸው በየዐውደ ምሕረቱ ቃል ባስተላለፉበት ወቅት ምእመናን ከሌላ ሰው የወሰዱትን እንዲመልሱ፣ ለሌላ ዘረፋና የንብረት ውድመት ተግባራ እንዳይሰማሩ ጭምር ሆነዋል፡፡ ችግሩ በከፍተኛ ደረጃ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?**

**መምህር ለይኩን፡-** በሀገራችን የተከሰተው ጦርነትና ችግር እውነተኛ የሆነ የመረዳዳት ዕሴቶቻችን እንድናይ አድርጎናል፡፡ የተቸገረን መርዳት የማንንም ቤት አያጎድልም፡፡ የመረዳዳት እሴቶቻችን መጠቀም ያለብን ችግር በገጠመን ወቅት ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም ቢሆን የተቸገሩ ወገኖችን ልናስብ ይገባል፡፡ ደግነትና አዛኝነት የሚለካው በተለይም በችግርና በመከራ ጊዜ ነውና እኛ ኢትዮጵያውያን በተለይም ኦርቶዶክሳውያን የመረዳዳትና ተካፍሎ የመብላት ባህላችንን አጎልብተን ልናስቀጥል ይገባል የሚል ወንድማዊ መልእክት አለኝ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለነበረን ቆይታ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ፡፡**

**መምህር ለይኩን ብርሃኑ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ዐበይት ነቢያት፤ ክፍል ሁለት፡- ነቢዩ ኤርምያስ

ምኒልክ ብርሃኑ

ልጆች! እንደምን ቆያችሁ? የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን እኛ በጣም ደኅና ነን፡፡ የዕረፍት ጊዜያችሁ እንዴት ነበር? ዕረፍታችሁንም መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ እንዳሳለፋችሁ እርግጠኞች ነን፡፡ አሁን ደግሞ ዕረፍታችሁን ጨርሳችሁ የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ትምህርት ልትጀምሩ ነው፡፡

ታዲያ ልጆች! በሁለተኛው ሴሚተር ካባለፈው የተሻለ ውጤት ለማምጣት በደንብ ማንበብ፣ ማጥናት አለባችሁ፡፡ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን እና ኢትዮጵያን የምተረከቡ በመሆናችሁ በርትታችሁ በመማር ጥሩ ቦታ መድረስ ትችላላችሁ፡፡ ጎበዞች!!



ነቢዩ ኤርምያስ በልጅነቱ ሲያገለግል

ልጆች! በዛሬ ቆይታችን የምንማረው፣ ባለፈው የጀመርነውን የነቢያትን ታሪክ ቀጣዩን ክፍል ሁለትን ነው፡፡ በክፍል ሁለት የምናገኘው ደግሞ ነቢዩ ኤርምያስን ነው፡፡ ስለ ነቢዩ ማንነት፣ ለነቢይነት እንዴት እንደተመረጠ፣ ያስተማራቸውን ትምህርቶች እና ዕረፍቱን በተመለከተ በደንብ እንማራለን ማለት ነው እናንተም በጥሙና እንድታነቡ እየጋበዝን መልካም ንባብን እንመኝላችኂለን፡፡

ልጆች! "ኤርምያስ" ከእብራይስጥ የተገኘ ቃል ሲኾን "እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያደርጋል" ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም "ብርሃን" ማለትም ነው፡፡ ከአራቱ ዐበይት ነቢያት አንዱ ሲኾን አባቱ "ኬልቅያስ" ይባላል፡፡

እናቱ ደግሞ "ማርታ" ትባላለች፡፡ አገሩ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ካለው ከተማ ዓናቶት በሚባል ቦታ ሲኾን ትውልዱም ከካህናት ወገን ከነገደ ሌዊ ነው፡፡ ዕድገቱ በኢየሩሳሌም ከተማ በቤተ መቅደስ ውስጥ ከልጅነቱ ጀምሮ ሕዝቡን እየገሠጸ ያስተምር ነበር፡፡ ሁልጊዜም ከቤተ መቅደስ አይለይም ነበር፡፡

ልጆች! ነቢዩ ኤርምያስ ለነቢይነት የተመረጠውና የተጠራው ገና በሕፃንነቱ ሳለ ነበር፡፡ ለነቢይነት የተጠራበት ዘመን ደግሞ በ፮፻፳፮ ቅ.ል.ክ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮስያስ በነገሠ በ፲፫ኛው ዓመት ነው፡፡ ነገር ግን በጣም ሕፃን ስለነበር ይፈራ ነበር፡፡ ኾኖም እግዚአብሔር እንደማይለየው እና በሥራው ሁሉ እንደሚረዳው፣ የሚፈራውም አንዳች ነገር ሊኖር እንደማይገባ ነገረው፡፡

ኤርምያስም እግዚአብሔር በሰጠው ቃል መሠረት ወደ አገልግሎቱ ገባ፡፡ ከዚያም ትንቢት እየተናገረ፣ ሕዝቡንም እያስተማረና እየመከረ ቆየ፡፡

ልጆች! ነቢዩ ኤርምያስ ትንቢቱን የተናገረው በንጉሡ ኢዮስያስ፣በንጉሡ ኢዮአክስ፣ በንጉሡ ኢዮቄምና በንጉሡ ኢኮንያን ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ ታዲያ በዚያን ዘመን የእሥራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ረስተው፣ ትእዛዙንና ሕጉን ትተው የኃጢአት ሥራ አብዝተው ነበር፡፡

በኋላም ነቢዩ ኤርምያስ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ያስተምራቸው ነበር፡፡ የማይመለሱ ከሆነ ደግሞ በጦርነት ተማርከው ወደ ባቢሎን ሀገር እንደሚወሰዱ፤ እስከ ፸

ዘመን እንደማይመለሱም ትንቢት ነገራቸው፡፡ እነርሱ ግን ምንም አልሰሙትም፡፡ በንስሓ ከመመለስ ይልቅ ከሕዝቡ እስከ ንጉሡ ድረስ ያሉት በሙሉ ብዙዎች ይጠሉትም ጀመር፡፡ ሊገድሉት ያስቡ ነበር፡፡



ነቢዩ ኤርምያስ የኢየሩሳሌም ሰዎች በስደት ሳሉ እንዳስተማረ

ልጆች! አያችሁ አይደል የሕዝቡን ጥፋት! በንስሓ ተመለሱ፤ ከመጥፎ ሥራ ተከልከሉ ብሎ ቢመክራቸው፣ ቢገሥጻቸው አልሰሙትም፡፡ ተፀፅተው ከመመለስ ይልቅ፣ የሚመክራቸውን ነቢዩ ኤርምያስን ቂም በመያዝ ጠሉት፡፡ ሊገድሉትም ፈለጉት፡፡ እናንተ ግን እንደዚህ እንደማታደርጉ እርግጠኞች ነን፡፡

ታላላቅ ሰዎች የሚነግሯችሁን መስማት እና መቀበል አለባችሁ፡፡ ካለበለዚያ እግዚአብሔር ያዝንብንና ይቆጣናል፡፡

ታዲያ ልጆች! ከብዙ ጊዜያት በኋላ የኢየሩሳሌም ሰዎች በጦርነት ተማርከው ወደ ባቢሎን ሀገር ተሰደዱ፤ በባርነት መኖር ጀመሩ፡፡ በስደትም ሳሉ እግዚአብሔር አምላክ ወደ ሀገራቸው እንደሚመልሳቸው ያፅናናቸው ነበር፡፡ ነቢዩ ኤርምያስ የኢየሩሳሌም ሕዝብን ከመማረካቸው በፊት ለ፵ ዓመታት፤ በባቢሎን ከተማረኩ በኋላ ደግሞ ለ፳ ዓመታት፤ በአጠቃላይ ለ፮፲ ዓመታት በነቢይነት እና በመምህርነት አገልግሏል፡፡

ብዙ ሥቃይና እስራት ደርሶበታል፡፡ እጅግ ጥልቅ ወደሆነ ቆሻሻ ወደሚጣልበት ጉድጓድ ውስጥ ጥለውት ያውቃሉ፡፡ በእሥር ቤትም ብዙ ጊዜ ይደበድቡት ነበር፡፡ እግዚአብሔር የገለጠለትን ትንቢት በመናገሩ ክፉዎችም ሊገድሉት ያስቡ ነበር፡፡

በዚህም ምክንያት ብዙ መከራና ብዙ ሥቃይ አደረሱበት፡፡ በስተመጨረሻም በድንጋይ ወግረውት ገደሉት፡፡ በሰማዕትነትም ዐረፈ፡፡ ለክብሩ መታሰቢያ ግንቦት ፩ በየዓመቱ ስሙ ይዘከራል፡፡

ልጆች! የነቢዩ ኤርምያስ መጽሐፍ "ትንቢተ ኤርምያስ"ይሰኛል፡፡ ፶፪ምዕራፎችንና ፲፮፴፮፳፫ (፲፫፳፫) ቁጥሮችን በውስጡ ይዟል፡፡ የመጽሐፉ ይዘትም ሕዝቡ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ እንዳያመልኩና ተታለው የነበሩም ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ መስበክ፤ ሰዎችን ወደ ንስሓ መጥራት፣ ተስፋ በመስጠትና በማጽናናት ከመጥፎ ድርጊቶች እንዲቆጠቡ ማስተማር ነው፡፡

ልጆች! ከዚህ ታሪክ የምንማረው እግዚአብሔር በሰዎች ላይ አድሮ ሲገስፀን መቀበል እንዳለብን፤ ከጥፋታችንም ተምረን ንስሓ መግባት እንደሚገባን፤ ጥፋት ያጠፋ ሰው እንደሚቀጣ፤ እግዚአብሔር አምላካችንን ብቻ ማምለክ እንዳለብን እንማራለን፡፡

በሉ ልጆች! ለዛሬ በዚህ ይብቃን፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ በክፍል ሦስት እስከምንገናኝ ደኅና ሁኑ ልጆች! ደኅና ሁኑ!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

**ምንጭ፡-** የትንቢተ ዳንኤል አንድምታ መቅድም፣ በሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ የተዘጋጀ፤ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣መምህር ቸርነት አበበ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣

# ከመዝሙር አገልግሎት ባሻገር

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙ የፈተና ዘመናትን አሳልፋለች፡፡ በርካታ የመከራ ዘመናትንም ተሻግራለች፡፡ የአባቶቻችንን እምነትና የእምነት ጽንዓት አክብራ፣ ጠብቃ ለትውልድ አሻግራለች፡፡ የአሁኑ ዘመን ትውልድም ይህንኑ መንገድ ተከትሎ የቤተ ክርስቲያንን የአገልግሎት ታሪክ ወደ ቀጣዩ ዘመን የማሻገር ከባድ ኃላፊነት ወድቆበታል፡፡

ይህ ኃላፊነት ከወደቀባቸው ወሳኝ የአገልግሎት ሚና ካላቸው የቤተ ክርስቲያን ልጆች መካካል ደግሞ የሰንበት ተማሪዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ሰንበት ትምህርት ቤቶችና የሰንበት ትምህርት ቤቶች አገልግሎት እንዲስፋፋ የፈለገችበት ዋነኛው ምክንያትም ወቅቱን የዋጀ አገልግሎት ለዘመኑ ክርስቲያን ምእመናን በማቅረብ በኩል ሰንበት ትምህርት ቤቶች ወሳኝ ድርሻ አላቸው ብላ በማመን ነው፡፡

የአሁኑ ዘመን ደግሞ ከየትኛውም ጊዜ በላይ እጅግ ረቂቅና ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች የበዙበት ዘመን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም በግልጽ በአደባባይ እየተፈተነች ነው፡፡ ልጆቿም በየሥፍራው የሚገደሉበት፣ በግልጽ እንዲከፋፉሉ የሚገደዱበት፣ ቅርሶቿ የሚወድሙበት፣ በፖለቲከኞችም በዓይነ ቁራኛ የሚታዩበት፣ ታሪክ የሚበረዝበት፣ ከሀገር ውስጥ እስከ ዓለም አቀፍ ድረስ በብዙ መከራ እየተፈተነች ያለበት ወቅት ሆኗል፡፡

ይሁን እንጂ ይህንን ፈተና የሚመጥን ግብረ መልስ ለመስጠት ከመዘጋጀት አንጻር ብዙ የሚቀር ነገር እንዳለ በቀላሉ የምንታዘበው እየሆነ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አካላት ድርሻ ቢሆንም አስቀድመን የጠቀስናቸው የሰንበት ትምህርት ቤቶች ድርሻ ደግሞ በታሪክ አጋጣሚ ከፍተኛ ሆኗል፡፡

ሰንበት ትምህርት ቤቶች የተማሩ፣ አፍላ፣ ንቁ፣ ዘመኑን የሚዋጁ ወጣቶች የተሰበሰቡባቸው ከመሆናቸው አንጻር ቤተ ክርስቲያን የተደቀነባትን ፈተና ለመወጣትና ለቀጣይ ዘመን ለማሻገር ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ አገልግሎታቸውን ከትናንት በተሻለና በተለየ መንገድ ማደራጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የዛሬ ፈተና ከትናንት የተለየ እየሆነ ነው፡፡ ስለዚህ የአገልግሎታችን ሥነ ዘዴም ከትናንት የተለየ እንዲሆን ያስገድደዋል፡፡

ከከተማ እስከ ገጠር ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን አጥብቀው የያዙት የመዝሙር አገልግሎት ብቻ ፈተናውን እንድንሻገር አያደርገንም፡፡ ዝማሬ የማይቀር፣ ጸሎትም ትምህርትም ምስጋናም ነው፡፡ ከዚህ በላይ ከፍለን በሌላ የመማርና የማስተማር ሥነዘዴ ተግተን መገኘት ያስፈልጋል፡፡

ሰንበት ትምህርት ቤቶች የዘመኑን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው፣ የዘመኑን መንፈስ የተገነዘቡ ሆነው፣ ፈጣን ሆነው፣ ተቀናጅተው፣ ተባብረው፣ ተፋቅረው፣ ተገነዛዝበው እንዲያገለግሉ ይፈለጋል፡፡ የሰይጣን የፈተና ዘይቤም ምን እንደሚመስል ተረድቶ ማገልገል ይጠበቅባቸዋል፡፡

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጣዊ ድክመቶች ምን እንደሆኑ ለይቶ እነሱን ቀርፎ ጠንካራ የአገልግሎት አፈጻጸም እንዲመጣ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ውጫዊ ስጋቶቻችን ምንድናቸው ተብለውም መተንተን አለባቸው፡፡ ሰይጣን ያሉትን የቤተ ክርስቲያን ጠላቶችን ሁሉ እንዳዘመተብን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ በዚህም የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ያልተረዱ ፖለቲከኞች ለሰይጣን መጠቀሚያ እየሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም በክርስቶስ ያለንን ፍቅርና አንድነት ለመፈተን እጅግ ረቂቅ የመለያየት ሴራ ዘርግቷል፡፡ በዘር፣ በቋንቋ፣ በባህልና በፖለቲካ አመለካካትም ቤተ ክርስቲያን ፈተና ውስጥ እንድትገባ እየሠሩ ነው፡፡

በመሆኑም እኛ ከመፍዘዝ መውጣት አለብን፡፡ በመፍዘዛችን እርስ በእርስ ለመተዛዘብ እየተገደድን ነው፡፡ የሐዋርያትን ቃል እናስታውስ ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ

የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤›› ብሎናል (፩ኛ ጴጥ. ፭፥፰)፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ፥ ጎልምሱ ጠንክሩ፡፡›› ብሎናል (፩ኛ ቆሮ. ፲፮፥፲፫)፡፡

# ሰንበት ትምህርት ቤቶች የዘመኑን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው፣ የዘመኑን መንፈስ የተገነዘቡ ሆነው፣ ፈጣን ሆነው፣ ተቀናጅተው፣ ተባብረው፣ ተፋቅረው፣ ተገነዛዝበው እንዲያገለግሉ ይፈለጋል፡፡

ስለዚህ ወደፊት የምንሰጠው ግብረ መልስ ምን ይሁን? ምን ስልት እንከተል? ብሎ መምከር ከመዘመር ባሻገር የሚታሰብ አገልግሎት ነው፡፡ ምእመናን ከኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ የሚገለሉበት ስውር አካሄድ ሊዘረጋ እንደሚችል ብዙ ምልክቶች አሉ፡፡ ምእመናን ለሥራ ሳይልግሙ በዚህ ዓለም ሲኖሩ ባላቸው ጥበብ ሁሉ ለልጆቻቸውና ለራሳቸው ሠርተው የሚኖሩበትን የኢኮኖሚ ተሳትፎ በንቃት እንዲከታተሉ ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በፖለቲካና በልዩ ልዩ ተቋማት አመራርነት እንዳይሳተፉ የሚያሸማቅቁ አካሔዶች እየታዩ ስለሆነ በዚህ ረገድ ምእመናናን በሀገራቸው በነጻነት መኖር የሚያስችላቸው ፍቅር የተሞላበት የፖለቲካ ባህል ለመገንባት እንዲነሡ ማንቃት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ከመዘመር ባሻገር የሚጠበቅባቸው አገልግሎት ነው፡፡

ምእመናን በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ በሚዋከቡበት በዚህ ወቅት መናፍቃን የጥፋት ዘራቸውን እየዘሩ የቅሰጣ ሥራቸውን በማስፋፋት ላይ ናቸው፡፡ ለዚህም ቃለ እግዚአብሔርን ከመቼውም ጊዜ በላይ ጥበብ በተሞላበት መንገድ መስጠት፣ ማስፋፋት ከዚህ ዘመን ሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚጠበቅ ነው፡፡ በርካቶች በማስመሰል ሕይወት ተዘፍቀው፣ ለንስሓ ሕይወት ጀርባቸውን ሰጥተው እግዚአብሔርን በሚያሳዝኑበት በዚህ ወቅት ሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመዘመር አገልግሎት ምእመናን እውነተኛ የንስሐ ሕይወት እንዲኖሩ የማድረግ አገልግሎት አለባቸው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የዘመኑን የብዙኃን መገናኛ እና ማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮች ሁሉ በመጠቀም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ከጊዜ ወደጊዜ የሚጎዳ ጫና እያሳደሩ ነው፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ዘመኑን በዋጀ መረጃ፣ ተግባቦትና ቴክኖሎጂ በንቃትና በስፋት በመጠቀም ለዚህ አጥፊ ዘመቻ ምላሽ የሚሆን አገልግሎት በሚገባ ይዘው መገኘት አለባቸው፡፡ ከዚህ ቴክኖሎጂ ሳንሸሽ አዎንታዊ ተፅዕኖ በመፍጠር ከጥፋት የምንመልሳቸውን በከንቱ የተሰለፉብንን ጠላቶች ከመግታት ባሻገር በዚያው የቴክኖሎጂ ዓለም ውስጥ ያሉ ምእመናንን በአገልግሎት ተደራሽ በማድረግ ዕድላችንን ያሰፋል፡፡ ‹‹ዘመኑን እየዋጃችሁ፥ በውጭ ባሉቱ ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ፡፡›› ያለውን ቃል ልብ ይሏል፡፡ (ቆላ ፬፥፭)

በአጠቃላይ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አገልግሎት በሁሉም መስክ በአጭር ጊዜ እመርታዊ ለውጥ ካላሳየ እንዲሁም በሚገባው መጠን መሮጥ ካልቻለ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ሊያሻግር አይችልምና ዘመኑን ለመዋጀት ይታሰብበት እንላለን፡፡

# ኀዘኑ ሊወጣልኝ አልቻለም

*ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች እንደምን ከረማችሁ? ሕይወቴን እጅግ የከበደውንና ከልቤ አልጠፋ ያለውን ሐዘን ሳካፍላችሁ የመፍትሔ ሐሳብ እንድትሰጡኝ በማመን ጭምር ነው፡፡ ዛሬ ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ በውል ትረዳላችሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ብዙ ሰዎች በብዙ መከራና ሐዘን ውስጥ እንደሆኑ አውቃለሁ፡፡*

*ነገር ግን በእኔ ላይ የወደቀው የሐዘን ሸክም ከምሸከመው በላይ ሆኖብኛል፡፡ ባለቤቴን በወጣበት ሳይመለስ ጨካኞች ቀጥቅጠው ገድለውብኛል፡፡ እኔ እስከማውቀው ባለቤቴ ከሃይማኖታዊ ሕይወቱ በስተቀር በዚህ ሀገር ላለ የፖለቲካ ወሬ ቦታ አልነበረውም፡፡ ንጽህናውን እያወቁ ለምን እንደገደሉት ሳስብ አይገባኝም፡፡ እኔ እስከ አሁን ማመን አቅቶኛል፡፡ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለልጆቹም ለመቀበል ከብዷቸዋል፡፡ በውስጤ ያለውን የሐዘን ስሜትም ሳዳምጠው ብርቱ ነው፡፡ ፡ስድስት ወራት ቢሆነውም ሞቱን የሰማሁበትንና ያየሁትን ዕለትና የተሰማኝን ድንጋጤ ሳስበው በውስጤ ይመላለሳል፡፡ እንዴት ይውጣልኝ? እባካችሁ አዋዩኝ፡፡*

ውድ ጠያቂያችን አሁን አሁን በኢትዮጵያ እርስዎን የመሰሉ በከፍተኛ ሐዘን ልባቸው የተሰበረ ወንድሞችና እኅቶች እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ሀገራችን ካጋጠማት ብርቱ የፖለቲካ ቀውስ የተነሣ ባልተጠበቁ ሁከትና ትርምሶች፣ በጦርነትና በከፍተኛ ሰው ሠራሽ አደጋዎች፣ በዘራፊዎችና ልዩ ልዩ ፍላጎት ባላቸው ወንበዴዎች የሚወዷቸውን ወገኖቻቸውን እያጡ መሆኑን እናውቃለን፡፡ ከዚህ የተነሣም በሞት የተለዩአቸውን የሚያውቁ እርስዎን የመሰሉ ዘመዶቻቸው ወገኖቻቸው ብቻ ሳይሆኑ እያንዳንዱ የርኅራኄ ልብ ያልተለየው ክርስቲያን ወገን ሁሉ በሐዘን እየተመታ ነው፡፡ እኛ ሁላችን ስለዚህ ነገር ልባችን ይደማል፡፡

ሞት እንግዳ ባይሆንም ባልተጠበቀ ሁኔታና በጨካኞች እጅ በድንገት የሚወዷቸውን ማጣት በእጅጉ የሚያም ነው፡፡ ለሰውም ከሞቱ ይልቅ አሟሟቱ በምድር ላይ ለጊዜው ለቀሩት ወገኖች የሚሰጠው ትርጉም አለ፡፡ ድንገተኛ በሆኑና በጨካኞች እጅ በሚፈጸም ግድያ ምክንያት የሚሞት ሰው ሁኔታ ግን ከማበሳጨቱና ከማስደንገጡ የተነሣ ሐዘኑም የከፋ ነው፡፡ ለብዙዎችም የማይሽከሙት፣ የማያምኑት፣ ሕልም እስኪመስላቸው የሚደናገሩበት ሆኖ እየታየ ነው፡፡ ለአንዳንዶቹ መሞታቸው ብቻ ሳይሆን አሟሟታቸው፣ አሟሟታቸው ብቻም ሳይሆን ከሞቱ በኋላ አካላቸው ላይ የሚደርስ ክብር ማሳጣት፣ ከእነጭራሹም የት እንደወደቁ አለመታወቅ እንኳን በቅርበት ለሚያውቋቸው በብዙኃን መገናኛ ወይም በማኅበራዊ ሚዲያ ለሚያዩና ለሚሰሙ እንኳን እንቅልፍ የሚያሳጣ ነው፡፡

ውድ ጠያቂያችንን ይህንን የምንልዎ ሐዘንዎን ለማባባስ ሳይሆን ብዙዎች በዚህ ቅዠት በሚመስል ነገር ግን እውነተኛ ሐዘን ሰቆቃ ውስጥ እያለፉ መሆኑን እንዲገነዘቡ ለማሳሰብ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ ለአማኝ ክርስቲያኖች የሚበረታ ሐዘን ከሆነ፣ ከዚህ ዓለም በቀር ተስፋ እንደሌላቸው ለሚያስቡ ኢ-አማንያን ደግሞ ምን ያህል የሚያውክ እንደሆነ አስቡት፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ከሐዘንዎ ለመጽናናት የሚያነቃዎ አንድ ቃል በማስነበብ እንዲያስተውሉ ልናበረታታዎ እንወዳለን፡፡ እርስዎ ክርስቲያን እንደ መሆንዎ እጅግ የታመነ፣ የተወደደ፣ አሸናፊ፣ ሩኅሩህና ብርቱ ጌታ አለዎት፡፡ እርሱም ሞትን ድል ያደረገ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱም እንዲህ ይላል ‹‹ኢየሱስም፦ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤›› (ዮሐ. ፲፩፥፳፭) ይህ በእውነት ለሚያምኑ ክርስቲያኖች ሐዘን ባጋጠማቸው ጊዜ ሁሉ የሚፈወሱበት ታላቅ ቃል ነው፡፡ ጌታችን ቢሞትም እንኳን ሕያው ይሆናል ያለው ቃሉ ሰዎች በሥጋ የመሞታቸው ነገር የማይቀር መሆኑን አስበው ከሐዘናቸው የሚበረቱበት ብቻ ሳይሆን ከማይቀረው ሞት መዳፍ የሚያስነሣ አሸናፊውን ክርስቶስን አምነው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው መኖራቸውን ባሰቡ ጊዜ ሁሉ የሚበረታቱበትም ነው፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ሐዘን ቀላል እንደሆነ እየነገርንዎት አይደለም፤ ከዚያ የምንነሣበት ደስታ ተስፋም ያለን መሆናችንንም እንዲያስቡት እንጂ፡፡ ይህ ከሐዘንዎ ለመውጣት ደጋግመው ሊያስቡት የሚገባ ነጥብ ነው፡፡ በዘመነ ብሉይ ከነበሩ ብርቱ ሐዘኖች ያዕቆብን ማሰብ ይቻላል፡፡

የሚወደው ልጁ ሳይሞት እንደሞተ ተደርጎ ተነግሮት ከእኛ ዘመን የዕድሜ ዕድል አንጻር ቀላል ቁጥር ያልነበረውን ዘመኑን በሐዘን መጨረሱን አስታውሱ፡፡ ያዕቆብ ከሐዘኑ የከፋው ደግሞ ልጁን በክብር ሳይቀብረው እንኳን አውሬ እንደበላው ልጆቹ የነገሩትን ቃል አምኖ ደም የተነከረ ልብስን ብቻ ይዞ ማንባቱን አስታውሱ፡፡ (ዘፍ.፴፯፥፩፴፯)

በኋላ ደግሞ ምስጢሩን በልቧ ትጠብቀው የነበረ ቢሆንም በድንግል ማርያም ላይ የደረሰውን ሐዘን አስተውሉ፤ ቅድስት ድንግል ልጇ ከተወለደ ጀምሮ ሐዘን በትር እንደሚመታት በትንቢት ተነገሯት ከዛሬ ነገ እያለች ከልጇ ከስደቱ እስከ ስቅላቱ ቀን ሁሉ በሰቀቀን ኖራለች፡፡ ልጇ በአይሁድ እጅ ከወደቀ በኋላ ያዕቆብ ያገኘውን ያህል የሐዘን መጽናናት ክብር እንኳን ተነፍጋ ነበር፡፡ ያዕቆብ ያገኘውን ያህል የልጇን ልብስ እንኳን ይዛ ማልቀስ አልቻለችም ነበርና፡፡ የልጇንም ልብስ አይሁድ በዕጣ እስከ መካፈል ደረሰዋልና፡፡ የልጇን ሥጋ በጠባቂዎች አስጠብቀው፣ መቃብር በዘበኛ አስከልለው ዕንባዋን እንኳን ቀርባ የምታፈስበት አልነበራትም፡፡

ውድ ጠቂያችን! ለትእግሥትና ለመጽናናት ምሳሌ የሚሆነንን ታላቁን ሰው ኢዮብንም አስቡት፡፡ ኢዮብ ልጆቹን ሁሉ በአንድ ጊዜ ያጣበትን የኀዘን በትር አስታውሱ፡፡ በኋላ ያዕቆብ በዮሴፍ መገኘት፣ ኢዮብም በሌሎች መልካም ልጆች መባረክ፣ ድንግል ማርያምም በልጇ በመድኃኔ ዓለም ትንሣኤ ያገኙትን መጽናናትና ደስታ ሳያዩ አስቀድመው ግን የተሸከሙትን ሐዘን አስተውሉ፡፡

ውድ ጠቂያችን! እውነት ነው በሰው ላይ የሚደርስ የግፍ ግድያ ለኀዘኑ ባለቤት ከባድ ሸክም ነው፡፡ እርስዎም ባለቤትዎ ላይ የደረሰው የግፍ ግድያ እንዴት ሊያም እንደሚችል እንረዳለን፡፡ እርስዎ ግን በወንድሙ እጅ በግፍ የተገደለውን አቤልን ደም የተበቀለ እግዚአብሔርን አስቡ፡፡ በቤተመቅደስ በጭካኔ በአሁድ እጅ በከንቱ የፈሰሰውን የካህኑን የዘካርያስን ደም የተበቀለ ጌታን አስቡ፡፡ የንጹሓን ደም ተመልካች አለው፡፡ ጌታችን ‹‹ከአቤል ደም ጀምሮ በመሠዊያውና በቤተ መቅደስ መካከል እስከ ጠፋው እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ፥ ከዚህ ትውልድ

እንዲፈለግ አዎን እላችኋለሁ፥ ከዚህ ትውልድ ይፈለጋል፡፡››(ሉቃ. ፲፩፥፶፩) ያለውን ቃሉን እናስታውስ፡፡

ውድ ጠቂያችን! እርስዎ ክርስቲያን ነዎት የክርስትና እምነት መሠረት ደግሞ የሙታን ትንሣኤን በማመን ላይ ነው፡፡ እርሱም የእምነታችን ኃይልና ተስፋ ነው፡፡ ሐዋርያው የተናገረውን ቃልም ያስተውሱ፤ ‹‹ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን፡፡ ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና፡፡ በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤ ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን፡፡ ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ፡፡(፩ኛ ተሰ ፬፥ ፲፫)

ይህ የሚያመለክተው ክርስቲኖችም በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት የማይቀረውን ሞት ይቀበላሉ፡፡ ነገር ግን ሞትን የሚቀበሉት፣ ቀሪዎችም ከዚህ ዓለም በሞት ስላለፈ ወገናቸው የሚያዝኑት ኀዘን በቀቢጸ ተስፋ የተዋጠ እንዳይሆን በመጠንቀቅ ነው፡፡ በሞታቸው እናዝናለን ስንል በተስፋ ደግሞ እንጽናናለን ጠቢቡም ‹‹ለማልቀስ ጊዜ አለው፥ ለመሳቅም ጊዜ አለው፤›› (መክ ፫፥፬) ያለውን ቃል በማሰብ ምክንያታዊ ኀዘንን ምክንያታዊ ለሆነ ጊዜ ብቻ መያዝ ያስፈልጋል፡፡

ውድ ጠቂያችን! ከኀዘን ለመጽናናት ማሰብ ያለብዎ የሚቱን ተስፋ ትንሣኤ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ዓለም ተለየ የማለት ትርጉምንም ነው፡፡ ከዚህ ዓለም አንድ ሰው በሞት ሲያልፍ ‹‹ዐረፈ›› የሚባለው ይህ ዓለም ስቃይ፣ የድካም፣ የክህደት፣ የሁከት፣ የጨካኞች፣ የስስታሞች…ወዘተ ዓለም ስለሆነ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ አዋኪ ነገር መለየታቸውን ማሰብም ያስፈልጋል፡፡ በተለይ በዚህ አስቀያሚ ዘመን ደግሞ ሞትን አማሮ መገኘት የራሱ አወያይነት አለው፡፡ የሞተው ሰው ግን በእርግጥም ከዚህ ሁሉ የኃጢአት ትብትብ ወጥመድ መገላገሉን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ‹‹ዕንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአል›› (ራዕ ፳፩፥ ፬) የተባለው በምጽአት ያለ ተስፋ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ነፍሳቸው በአምላካቸው ክንድ ውስጥ ላረፈች ነፍሳት ሁሉ ነው፡፡

ስለዚህ በታሪክ ዘመን ውስጥ በርካታ ክርስቲያኖች ክርስቲያን ልጆቻቸውን፣ እናትና አባታቸውን፣ የትዳር አጋራቸውን በሕመም ምክንያት ወይም በድንገት አጥተዋል፡፡ በጨካኞች በግፍ ተነጥቀዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔርን የፍርድና የተስፋ ቀን ስለሚጠብቁ ውለው አድረው ይጽናናሉ፡፡

ውድ ጠቂያችን! ከምንም በላይ መያዝ ያለብዎት ነገር ሰዎች በኀዘን መያዛቸው ያለ ነገር ሆኖ መጽናናትንም የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው፡፡ ኀዘን ከባድ ነው፤ የሕይወትም ፈተና ሆኖ ሊገለጥ ይችላል ከዚህ በኋላ ከፍተኛ የጤና መታወክና ራስንም እስከማጣት ለሚያደርስ መከራ ሊያጋልጥም ይችላል፡፡ በዚህ ውስጥ ሰይጣንም ወጥመድን ይዘረጋል፡፡ እምነትን ማሳጣቱ በክርስቶስ ያለ ተስፋን ማስካዱ ብቻ ሳይሆን ቀሪ ዕድሜን ሰላም የሚያሳጣ ደዌን ተክሎብን ይሄዳል፡፡ ስለዚህ መጽናናትን እግዚአብሔር እንዲሰጥ መጸለይ ሌላው የምንመክርዎ ነገር ነው፡፡

ስለዚህ ማዘን የሚገባም፤ ጌታችን ለአልዓዛር እንባውን ማፍሰሱን እናስታውሳለን፡፡ ነገር ግን በቃሉ የትንሣኤን ተስፋ በራሱ በአልዓዛር ሥጋ ባሳያቸው በእኅቶቹና በዚያ ቢታንያ አካባቢ ለነበሩ ሰዎች የሰጠው ደስታ መጽናናም ነው፡፡ (ዮሐ ፲፩፥ ፴፪)

ውድ ጠያቂያችን! ካነሡት ጥያቄ አንጻር ሌላው ሊያጽናናዎትና ሊያበረታዎት የሚገባው ነገር በዚህ ዓለም እንዲያድጉ ከሚቹ ስለተወለዱ ልጆቻቸው ነው፡፡ለልጆቹ ያሉት እርስዎ ነዎት፡፡ ስለዚህ በኀዘን ስብራት የተነሣ ራስዎን ጎድተው ቤተሰብዎንም እንዳይጎዱ ይጠንቀቁ፡፡ ይህ ልጆቻቸውንና ሌሎች ዘመዶቻቸውን ከማበርታቱም በላይ የሐዘንን ጊዜ ቆጥቦ በቁም ያሉ/በሕይወተ ሥጋ/ ወገኖቻቸውን ማበርታት መንከባከብ የበለጠ ዕረፍት ይሰጣል፡፡

ሌላው የሞተ ወገንዎ የሞተበት ምክንያት ሊያጽናናዎት ይገባል፡፡ እጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ ሞት በኃጢአት ተጠምዶ ለኃጢአት መሞት ነው፡፡ ሲሰርቁ፣ ሲቀሙ፣ ሰውን ሲደፍሩ፣ ሲሰስቱ፣ ሌላወን ሲገድሉ ሲሸምቁ…መሞት ያሳፍራል፡፡ በግፈኞች እጅ መሞት ግን ያሳዝናል እንጅ ተስፋ አያስቆርጥም፡፡ እግዚአብሔር የብዙ ደጋግ ሰዎችን ነፍስ ተቀብሏል፡፡ ግፈኞችንም በምናስተውለውና በማናስተውለው መንገድ ይበቀላል፡፡

ሌላው ወሳኙ መጽናናት ለሟች ወገንዎ በምድር ላይ ሆነው በፍቅር የሚያደርጉለት መታሰቢያ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን በካህናቱ ጸሎት እንዲታሰብ፣ እግዚአብሔር ነፍሱን በገነት እንዲያሳርፍ እርስዎና ወዳጆቻቸው ሁሉ የሚያደርጉላቸው ጸሎት፣ ‹‹ነፍስ ይማር!›› እያሉ መልካሙን የሚመኙላቸው የተዝካራቸውን ጠበል ጠዲቅ የሚበሉ ነዳያን ቃል ሁሉ ሊያጽናናዎት ይገባል፡፡

በብርቱ የሚያጽናናውን ልበ አምላክ የተባለ የዳዊትን ሕይወትም ያስታውሱ፡፡ ዳዊት ከቤርሳቤህ የወለደው ህፃን በአርሱ ኃጢአት ምክንያት በታመመ ጊዜ አንዲድን በብዙ አዘነ ጸለየም ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍርድ ስለነበር ህፃኑ ከዚህ ዓለም አለፈ፡፡ በዚህ ጊዜ ክቡር ዳዊት ከምድር ተነሥቶ ታጠበ፥ ተቀባም፥ ልብሱንም ለወጠ፤ ወደ እግዚአብሔርም ቤት ገብቶ ሰገደ፡፡ ወደ ቤቱም መጣ፡፡ እንጀራም አምጡልኝ አለ በፊቱም አቀረቡለት፥ በላም ከዚያም ይህን ቃል ተናገረ ‹‹አሁን ግን ሞቶአል፤ የምጾመው ስለ ምንድር ነው? በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን? እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም›› (፪ኛ ሳሙ. ፲፪፥፳፫)፡፡

ውድ ጠቂያችን! እርስዎ በኀዘን የተጎዱባቸው ሰው የሄዱት ወደ እነዳዊትን የመሰሉ ብርቱ አባቶች ወዳሉበት፣ በግፍ የተገደሉ የእነ አቤል፣ የእነ ዘካርያስ፣ የእነ ቅዱስ እስጢፋኖስ ነፍሳት ወዳሉበት፣ በኀዘን መከራ የተሰቀቁ የእነ ያዕቆብ፣ የእነ ኢዮብ ነፍሳት ወዳሉበት፣ ስለልጇ በአምስቱ ኀዘናት የተቃጠለች ድንግል ማርያም በክብር ወዳለችበት ሥፍራ ከሁሉም በላይ ሞትን ያሸነፈ ንጉሣችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዙፋን ወደሚታይበት መንፈሳዊ፣ ሰማያዊ ቦታ ነውና ይህን አስበው ይጽናኑ እንላለን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡